# የመገናኛ ብዙሀን
# የግጭት ሙያዊ አዘጋገብ መርሆዎች

ህዳር 2015
አዲስ አበባ- ኢትዮጵያ

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| አስተዋጽኦ | 2 |
| መግቢያ | 3 |
| የሰነዱ ዓላማ | 3 |
| የሰነዱ ተጠቃሚዎች | 3 |
| የሰነዱ አስፈላጊነት | 4 |
| የሰነዱ አዘገጃጀት | 4 |
| ሥነዘዴ | 5 |
| የመርሆዎቹ አጠቃቀም | 5 |
| መርህ 1 - ከተለመደው አሰራር ውጡ | 6 |
| መርህ 2 - ስለ ግጭት ባህሪ አውቃችሁ አሳውቁ | 7 |
| መርህ 3 - ግጭት በራሱ መጥፎም ጥሩም አለመሆኑን ተረዱ | 9 |
| መርህ 4 - ግጭት ሂደት መሆኑን ተገንዘቡ | 10 |
| መርህ 5 - ለቀላል ማህበረሰባዊ ግጭቶች ትኩረት ስጡ | 11 |
| መርህ 6 - ስለ ግጭት ስትዘግቡ ነጻና ሚዛናዊ ሁኑ | 13 |
| መርህ 7 - የግጭት ዘገባዎቻችሁን አካታች አድርጉ | 15 |
| መርህ 8 - ከግጭት ዘገባ ምሉዕነት ጋር ሙያዊ ኃላፊነትን አስቡ | 16 |
| መርህ 9 - ስሜታዊና የተጋነኑ ቃላትን ከመጠቀም ተቆጠቡ | 17 |
| መርህ 10 - የጥላቻ ንግግሮችን አስወግዱ | 18 |
| መርህ 11 - የሀሰተኛ ዜናና መረጃ ስርጭትን ግቱ | 19 |
| መርህ 12 - የድህረ-ግጭት ጉዳዮችን ለማከም ትኩረት ስጡ | 21 |
| መርህ 13 - ውይይትና ምክክር አሳልጡ | 23 |
| መርህ 14 - ስለ ሰላም አውቃችሁ አሳውቁ | 25 |
| የቃላትና ሀረጎች መፍቻ | 27 |
| ማጣቀሻ ምንጮች | 28 |

# አስተዋጽኦ

ይህን ሰነድ ለማዘጋጀት ቁጥራቸው በርከት ያለ መስሪያ ቤቶች፣ የጋዜጠኞች ማህበራትና ተወካዮቻቸው ተሳትፈዋል፡፡ እንዲህ ባለ፣ አስተዋጽኦ በሚገለጽበት ገጽ ላይ የሁሉንም ተሳታፊዎች ስም በዝርዝር ማካተት ያልተለመደ ቢሆንም ለዚህ ሰነድ ዝግጅት ግን የተሳታፊዎች አበርክቶ ዋና ጉዳይና የባለድርሻነት ውክልና ስለሆነ ስማቸው ከነሚናቸው ተዘርዝሯል፡፡

ዶ/ር ተሻገር ሽፈራው (በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ት/ቤት መምህር) ሰነዱን በማርቀቅና በረቂቁ ላይ ጋዜጠኞች ካካሄዷቸው ሦስት ተከታታይ ውይይቶችና ከመስክ ጉብኝት የተገኙ ግብዓቶችን በየደረጃው አካቶ ሰነዱን ለህትመት በማዘጋጀት አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በሰነዱ ረቂቅ ላይ በሦስት ተከታታይ የውይይት መድረኮች ከተካሄዱ የቡድን ውይይቶች የተገኙ ዝርዝር የማሻሻያ ሀሳቦችን በጽሁፍ በማቅረብ ለሰነዱ የመጨረሻ መልክ መያዝ ከኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎች ማህበር፣ ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሙያ ሴቶች ማህበር፣ ከኢትዮጵያ አርታዕያን ማህበር፣ ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ምክር ቤት፣ ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለስልጣን፣ ከዴስቲኒ ኢትዮጵያና ከልዩ ልዩ መገናኛ ብዙሀን የተውጣጡ ባለሙያዎች ድርሻቸውን ተወጥተዋል፡፡

ኤፍሬም ተፈራ፣ ደረሰ ንጋቱ፣ ይታያል አጥናፉ፣ እመቤት ደመቀ፣ ኢሳያስ ፈቃዱ (ከኢትዮጵያ አርታዕያን ማህበር)፤ ርብቃ ታደሰ፣ የሸዋ ማስረሻ፣ መሰረት ከበደ፣ ቆንጂት ዘውዴ፣ ቅድስት ክፍለዮሀንስ (ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ሴቶች ማህበር)፤ ሰብስቤ ከበደ፣ ታምራት ኃይሉ፣ መሰረት አታላይ (ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ም/ቤት)፤ ዶ/ር እንዳሻው ወልደሚካዔል (ከኢትዮጵያ ብሮድካስተሮች ዘርፍ ማህበር)፣ ሰሎሞን ሙጩ፣ ሲሳይ ሳህሉ፣ መርሻ ጥሩነህ፣ ማናዬ እውነቴ፣ ተሾመ ኃይሉ፣ ሊዲያ ተስፋዬ፣ ካሳዬ ዳምጤ፣ እታገኘሁ መኮንን፣ ዳዊት በጋሻው፣ ዳዊት አስታጥቄ፣ ዳዊት አርኣያ፣ ዮዲት ሽፈራው (ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎች ማህበር) በሰነዱ ዝግጅት ላይ ተካፍለዋል፡፡

ሰሎሜ ደስታ፣ መታገስ ተሾመ፣ ኤርሚያስ ግዛው፣ አዲስ መሐመድ (ከግል መገናኛ ብዙሀን)፣ ትዕይንት ደባልቄ (ከሀረሪ መገናኛ ብዙሀን ድርጅት)፣ ሳሙዔል አባተ (ከቲቪ 9)፣ አስማን መሐመድ (ከአዲስ ምዕራፍ መጽሄት)፣ ናትናዔል ጌቾ (ከወላይታ ታይምስ)፣ ሀናን ሚፍታህ (ከአሀዱ ሬድዮ)፣ ግርማይ ከበደ (ከኢ.ቢ.ኤስ.) በልስቲ ዓለምነህ (ከኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት)፣ አርዓያ ጌታቸው (ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት)፣ ዓለማየሁ ጌታቸው (ከኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ጋዜጠኞች ማህበር)፣ አብረሀም ነጋሽ (ከሀመር ሚዲያ) በሰነዱ ዝግጅት ተሳትፈዋል፡፡

ግዛው ተስፋዬ፣ ቆንጂት ታምራት፣ ዱረቲ ታደሰ፣ ዴሬሳ ተረፈ፣ ገዛኸኝ ተክለስላሴ፣ አበራ ወንድወሰን፣ ደሴ ከፋለ፣ ሰላማዊት ፈቃደ፣ መታገስ ጥጋቤ፣ ነብዩ ዮሐንስ፣ ማህሌት ደረጀ፣ ተስፋዬ ጌትነት፣ ወንድሜነህ አስራት፣ ላዕከ ፈቀደ፣ ግራ ከንፉ፣ ዮሀመር ታደሰ (ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን)፣ እንዲሁም ዶ/ር ንጉሱ አክሊሉ፣ ወንድወሰን ስንታየሁና መስፍን ጌታቸው (ከዴስቲኒ ኢትዮጵያ) በሰነዱ ዝግጅት ድርሻቸውን ተወጥተዋል፡፡

## መግቢያ

የጋዜጠኝነት ሙያ የሚከተላቸው አጠቃላይ መርሆዎች አሉት፡፡ በመርሆዎቹ መሰረት ሙያው ተደራስያን የሚፈልጓቸውን ወቅታዊ የዜና ጥንቅሮችና በማህበረሰብ የእለት ተዕለት ህይወት ውስጥ ተጽዕኖ ያላቸውን ክስተቶች የሚመለከቱ ዘገባዎችን በእውነተኛና ትክክለኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ የማዘጋጀትና የማሰራጨት ተግባር ነው፡፡ የመገናኛ ብዙሀን ይዘቶች ሀላፊነትንና ተጠያቂነትን በሚያካትቱ ሙያዊ የአዘጋገብ መመዘኛዎች መሰረት እንዲሰናዱ ይጠበቃል፡፡

ስለ አንዳንድ ማህበረሰባዊ ጉዳዮች በምልዓት ለመዘገብ ጋዜጠኞች ከአጠቃላይ ሙያዊ መርሆዎች በተጨማሪ በተለያዩ የእውቀት መስኮች ላይ የተመሰረቱ የአዘጋገብ መርጃ ሰነዶች እንደሚያስፈልጓቸው ይታመናል፡፡ ከእነዚህም መካከል የማህበረሰብ ጤና፣ የሳይንስ፣ የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ፣ የውሀ፣ የግብርና፣ የምርመራ ዘገባ፣ የምርጫ፣ የፍርድ ቤት፣ የስርዓተጾታ፣ የግጭትና የሌሎች ዘርፎች አዘጋገብ መርጃ ሰነዶች ይገኙበታል፡፡

ግጭት በተወሳሰቡ ማህበረሰባዊ ምክንያቶች የሚፈጠርና የሰዎችን ህይወት አስቸጋሪ የሚያደርግ ፈታኝ ክስተት በመሆኑ የመገናኛ ብዙሀንን ትኩረት ይስባል፡፡ ዘገባዎችም ይቀርቡበታል፡፡ ሆኖም ብዙ ጥናቶች እንደሚያሳዩት የመገናኛ ብዙሀን የግጭት ዘገባዎች የበረቱ ችግሮች አሉባቸው፡፡

አንዳንድ መገናኛ ብዙሀን የማህበረሰባቸው ግጭት አካል ሆነው በወገንተኛነትና በጠላትነት አድሏዊና ግጭት አባባሽ የዜና ይዘቶችን እያመረቱ ያሰራጫሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ የጋራ መግባባት ለመፍጠር፣ ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትና ሰላምን ለመገንባት በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ያላቸው አዎንታዊ ሚና ዝቅተኛ ነው፡፡

ሆኖም ለግጭት ተጋላጭ በሆኑ ሀገሮች መገናኛ ብዙሀን ለሰላም መጠናከር የበኩላቸውን ሙያዊ ድርሻ እንዲወጡ ይጠበቃል፡፡ ይህ የመገናኛ ብዙሀን የግጭት ሙያዊ አዘጋገብ መርሆዎች በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሰነድ ትኩረት ከሚሹ አበይት ማህበረሰባዊ ክስተቶች አንዱ በሆነው ግጭትና የመገናኛ ብዙሀን አዎንታዊ ሚና ላይ ያተኩራል፡፡ ሰነዱ የግጭትና ሰላም መሰረታዊ ሀሳቦችንና ግጭትን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት መገናኛ ብዙሀን አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የሚያግዙ መርሆዎችን ይዟል፡፡

## የሰነዱ ዓላማ

ይህ ሰነድ የተዘጋጀው ጋዜጠኞች ስለ ግጭት ሲዘግቡ የሚያጋጥሟቸውን ልዩ ልዩ ሙያዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል እገዛ ለማበርከት ነው፡፡ ዓላማው የግጭት ዘገባ ከየእለቱ መደበኛ ዜና በተለየ ሁኔታ እውቀትና ክህሎት የሚጠይቅ በመሆኑ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ሰነዱ ጋዜጠኞች የመረጃ ምንጮችን ከማግኘት፣ መረጃ ከመሰብሰብ፣ ከመምረጥ፣ ሚዛናዊና የተሟላ ከማድረግ አንጻር ያሉባቸውን ችግሮች ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ በተወዛጋቢ ወገኖች መካከል መግባባትን ለመፍጠር የሚያስችል አዎንታዊ አስተዋጽኦ ከማበርከት አንጻር፤ እንዲሁም የዘገባ ይዘት በተደራስያንና በማህበረሰቡ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን አሉታዊ ተጽእኖ ከመቀነስ አኳያ ያሉባቸውን ፈተናዎች ይገነዘባል፡፡ ዓላማው እነዚህን ሙያዊ ተግዳሮቶቻቸውን መቋቋም እንዲችሉ መርዳት ነው፡፡

## የሰነዱ ተጠቃሚዎች

የሰነዱ ተጠቃሚዎች የህትመት፣ የሬድዮ፣ የቴሌቪዥንና የድረገጽ መገናኛ ብዙሀን ጋዜጠኞች ናቸው፡፡ በንግድ፣ በህዝብ (በመንግስት)፣ በማህበረሰብ እና በማናቸውም ምድብ ውስጥ ያሉ መገናኛ ብዙሀን ጋዜጠኞች ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ ሰነዱ በተለይ ከግጭትና ሰላም ዘገባ ጋር የተያያዙ አሻሚ ሙያዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያስችል እገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

## የሰነዱ አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀንና ጋዜጠኞች ከሚያጋጥሟቸው በርካታ ተግዳሮቶች መካከል የግጭት ሁነቶችንና የሰላም ጉዳዮችን ከመዘገብ ጋር የተያያዙት የበረቱ መሆናቸው በተደጋጋሚ ተገልጿል፡፡ ከሁሉም ወገን መረጃ ማግኘት፣ የመረጃ ትክክለኛነትንና እውነተኛነትን ማረጋገጥ፣ ከወገንተኝነት ነጻ የሆነ፣ ተኣማኒነት ያለው ወቅታዊ ዘገባ ከማቅረብ አንጻር ብዙ ጉድለቶች ይታያሉ፡፡

ግጭቶች አሳሳቢ የሀገር ችግር በሆኑበት አውድ ውስጥ መገናኛ ብዙሀን ለሰላማዊ መፍትሄ አስተዋጽኦ ከማበርከት አንጻር የተጫወቱት ሚና ከጥያቄዎች ነጻ አይደለም፡፡ የማይዘገቡ ግጭቶች አሉ፡፡ አንዳንዶች ተዛብተው ይቀርባሉ፡፡ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ግጭት አባባሽና ጎጂ የመረጃ ጥንቅሮችን የሚያሰራጩ መገናኛ ብዙሀንም መኖራቸውን የተለያዩ ጥናቶች ጠቁመዋል፡፡ በበረታ ወገንተኛነት፣ የጥላቻ ንግግሮችን፣ ሀሰተኛና የተዛቡ ዘገባዎችን የሚያሰራጩ መገናኛ ብዙሀን ይታያሉ፡፡

ልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሀን ማህበረሰብ አባላት በጋራ በመከሩባቸው መድረኮችም ስለ ግጭትና ሰላም የመዘገብ ተግባርን መደበኛው ጋዜጠኝነት በሚከተላቸው መርሆዎች ብቻ ለመወጣት እንደሚያስቸግር የሚጠቁሙ አስተያየቶች ተደጋግመዋል፡፡ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የተካሄዱ ውይይቶች ስለ ግጭት የሚዘግቡ ጋዜጠኞች ከወትሮ የተለየ ጥንቃቄና ኃላፊነት እንዳለባቸው አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡ የግጭትና ሰላም አዘጋገብ ክህሎት ቀርነት ከችግሮቹ መካከል ይገኛል፡፡ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ስለ ግጭትና ሰላም ለመዘገብ የሚያግዝ በመሰረታዊ ጽንሰ ሀሳቦች ላይ የተመሰረተ ሰነድ አስፈላጊ መሆኑን የተሰበሰቡት አስተያየቶች ይጠቁማሉ፡፡ በሰነዱ ዝግጅት ሂደት ከተሳታፊዎች የተሰበሰቡ አስተያየቶችም አስፈላጊነቱን አመልክተዋል፡፡

## የሰነዱ አዘገጃጀት

ይህ ሰነድ ለመገናኛ ብዙሀንና ጋዜጠኞች ሊያበረክት የሚችለው ሙያዊ እገዛ ከታመነበት በኋላ በሦስት የውይይት መድረኮች ከረቂቅ ዝግጅቱ ጀምሮ 60 ባለሙያዎች፣ ጋዜጠኞች፣ የጋዜጠኝነትና የመገናኛ ብዙሀን ማህበራት ተወካዮች በተገኙበት የሦስት ቀናት ውይይት ተካሂዶበታል፡፡ በቡድን የተከፋፈሉ ተሳታፊዎች በሰነዱ ውስጥ ካሉት አርዕስት ድርሻ ወስደው ከተወያዩባቸው በኋላ ባቀረቧቸው ግብረ መልሶች ላይ ተነጋግረው የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበዋል፡፡ ግብረመልሶቹ የሰነዱ ዝግጅት ዋነኛ ግብዓት ነበሩ፡፡

በተጨማሪም ለመገናኛ ብዙሀንና ጋዜጠኞች ሙያዊ የግጭት አዘጋገብ አቅም ለመፍጠር የተሻለ ተሞክሮ ካላት ኬንያ መረጃ ለማግኘት አንድ ቡድን በናይሮቢ የአንድ ሳምንት የልምድ ልውውጥ ጉብኝት አድርጓል፡፡ በጉብኝቱ ከኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎች ማህበር፣ ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሙያ ሴቶች ማህበር፣ ከአርታዕያን ማህበር፣ ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ምክር ቤት፣ ከኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለስልጣን፣ ከዴስቲኒ ኢትዮጵያና ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተውጣጡ ባለሙያዎች ተካፍለዋል፡፡

የቡድኑ አባላት በቆይታቸው ከኬንያ መገናኛ ብዙሀን ምክር ቤት፣ ከኮሚዩኒኬሽን ባለስልጣን፣ ከዘላቂ ሰላም ኮሚሽን፣ ከልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሀንና የጋዜጠኞች ማህበራት፣ ከሁለት የመረጃ ማጣሪያና ማመሳከሪያ ድርጅቶች ተወካዮችና ከአንድ የናይሮቢ አጋ ካህን ዩኒቨርስቲ የብዙሀን መገናኛ ትምህርት ፕሮፌሰር ጋር ተወያይተዋል፡፡ የተቋማቱ ተወካዮች ኬንያ በምርጫና ፖለቲካዊ አለመግባባት ምክንያት በተከሰቱ ነውጠኛ ግጭቶች ውስጥ አልፋ ወደ ሰላምና መግባባት ለመድረስ ስላከናወነቻቸው ተግባራት አስረድተዋል፡፡ በተለይም የአገሪቱ መገናኛ ብዙሀን ስለ ግጭት በሙያዊ ኃላፊነት በመዘገብ ለአገሪቱ ዘላቂ ሰላም አዎንታዊ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚያስችሏቸው ተከታታይ ስራዎች መስራታቸውን ገልጸዋል፡፡

የጋዜጠኞች የራስ-መቆጣጠሪያ ተቋማት፣ የሙያ ማህበራት፣ የመንግስት ተቆጣጣሪ አካልና የመገናኛ ብዙሀን ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች፣ ለዘላቂ ሰላም ከሚሰሩ ማዕከላት ጋር መግባባት ለመፍጠር ያካሄዷቸው የትብብር ስራዎችና ተከታታይ ውይይቶች በመካከላቸው ሰፍኖ የቆየውን አለመተማመን ለማስወገድ እንዳስቻላቸው አስረድተዋል፡፡

የአገሪቱ ልዩ ልዩ የጋዜጠኞች ማህበራት የግጭት አዘጋገብ ሙያዊ ሰነድ አዘጋጅተው እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡ ለሙያዊ ልህቀት የሚያግዙ ልዩ ልዩ ጥናቶች ተዘጋጅተው መገናኛ ብዙሀንና ጋዜጠኞች እንዲጠቀሙባቸው ያደርጋሉ፡፡

የተሞክሮ ልውውጥ ያደረገው ቡድን ከየማህበራቱ ለተውጣጡ ከሀምሳ በላይ ተሳታፊዎች ያገኘውን መረጃ በማካፈል በመገናኛ ብዙሀኑ ማህበረሰብ ሊከናወኑ ስለሚገባቸው ቀጣይ ተግባራት ተወያይቷል፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ ለውይይት በቀረበው የግጭት አዘጋገብ መርጃ ረቂቅ ሰነድ ውስጥ የጉብኝቱ ግብዓቶች ተካተው ከተወያዮች ግብረመልስ ተሰብስቧል፡፡ የተሰበሰቡ የማሻሻያ ሀሳቦችም ሰነዱን ለማዳበር ውለዋል፡፡

## ሥነዘዴ

የዚህ የመገናኛ ብዙሀን የግጭት አዘጋገብ አጋዥ ሰነድ ዝግጅት ስነዘዴ አራት ተግባሮችን በማጣመር ይዟል፡ ፡ የመጀመሪያው የሰላም ፣ የሰላም ግንባታ ፣ የግጭትና የግጭት አፈታት ጽንሰ ሀሳቦችን መገንዘብ ነው ፡፡ ይህም ከሰላም ጋር ተያያዥ የሆኑ ንድፈሀሳቦችንና አበይት መርሆዎችን በመዳሰስ የሰነዱን ይዘት ለመወሰን የሚያስችል ሀሳብ አስገኝቷል፡፡

ተከታዩ የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙሀንን የአርትኦት (ኤዲቶሪያል) ፖሊሲዎች በመዳሰስ ሰነዶቹ ውስጥ የግጭት አዘጋገብን በሚመለከት መገናኛ ብዙሀኑ ያካተቷቸውንና ተዛምዶ ያላቸውን አንቀጾች በመመልከት ጠቃሚ ሀሳቦችን ማግኘት ተችሏል፡፡

ሦስተኛው የተለያዩ ሀገሮች ጋዜጠኞች የሚጠቀሙባቸው የግጭት አዘጋገብ ሰነዶች ቅኝት ሰነዶቹ ያካተቷቸውን መርሆዎች ይዘትና ቅርጽ በመመልከት ለዚህ ሰነድ ዝግጅት የሚጠቅም ግብዓት የተገኘበት ነው፡፡ በሦስቱ ደረጃዎች በተዳሰሱት ይዘቶች ላይ በመመስረት የዚህ ሰነድ አንቀጾች በ14 መርሆዎች ተከፍለው ቀርበዋል፡፡

አራተኛው ስነዘዴ የመገናኛ ብዙሀን ባለድርሻዎች በተሳተፉባቸው ሦስት ተከታታይ የውይይት መድረኮች ሰነዱን በማስመርመር የተገኙ የማሻሻያ ግብዓቶችን አካትቶ በማዳበር የመጨረሻ የይዘትና የቅርጽ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ማድረግ ነው፡፡ ለመጨረሻው ውይይት በቀረበው ረቂቅ ሰነድ ውስጥ ከኬንያ መገናኛ ብዙሀን ጉብኝት የተገኘው ግብዓት የሰነዱ አካል ሆኗል፡፡

## የመርሆዎቹ አጠቃቀም

በዚህ ሰነድ ውስጥ 14 አብይት መርሆዎች አሉ፡፡ መርሆዎቹ በጋዜጠኝነት ሙያ ታዋቂ ከሆኑ የግጭት አዘጋገብ ጥናቶች፣ ምርምሮች፣ ሂሶችና በተለያዩ አገሮች ከተዘጋጁ የግጭት አዘጋገብ መርጃ ሰነዶች ውስጥ ለኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን አውድ እንዲስማሙ ተደርገው የተወሰዱ ናቸው፡፡

ከአውዱ ጋር የማስማማቱን ስራ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተደራጅተው በመስራት ላይ ካሉ ጋዜጠኞችና መገናኛ ብዙሀን ማህበራት እንዲሁም ባለድርሻዎች የተውጣጡ 60 ጋዜጠኞችና ባለሙያዎች በሦስት ዙር ውይይቶች ተሳትፈውበታል፡፡

በሰነዱ ውስጥ በተካተተው በእያንዳንዱ መርህ ስር «አጭር መግለጫ» እና «ተግባራት» የሚሉ አርዕስት ይገኛሉ፡፡ እያንዳንዱ አጭር መግለጫ በየተራ ቁጥሩ ስር የተቀመጡትን መርሆዎች ያብራራል፡፡ ለሙያ ህጸጾች ምክንያቶች የሆኑትን ችግሮች ይዘረዝራል፡፡ መፍትሄዎችን በምርምር ተቀባይነት ባገኙ ምንጮች ላይ ተመስርቶ ያቀርባል፡፡ «ተግባራት» በሚለው ርዕስ ደግሞ እያንዳንዱን መርህ ለመፈጸም የሚያስችሉ ክንውኖችን በነጥብ ለይቶ ያስቀምጣል፡፡

# መርህ 1
# ከተለመደው አሰራር ውጡ

## አጭር መግለጫ

ለግጭቶች፣ ለጦርነቶች፣ ለሰዎች እልቂት፣ ለውድመትና ለአደጋዎች ትኩረትና ቅድሚያ መስጠት የመገናኛ ብዙሀን ነባር ተሞክሮ ነው፡፡ በሙያዊ ጋዜጠኝነት ነውጥና ሁከት ቀዳሚ ዘገባ ይወጣዋል፡፡ የዚህ ልማድ መሰረታዊ ምክንያት በሰዎች ደህንነትና ጥቅም ላይ ከሚደርስ አደጋ የሚበልጥ ጉዳይ የለም የሚል ነው፡፡ የብዙዎችን ትኩረት የሚስብ፣ የሚያስደነግጥ፣ የሚያስፈራ፣ የሚያሳስብና ስጋት ውስጥ የሚጥል ጉዳይ ቀዳሚ ዜና ነው፡ ዓለም በውስጧ ብዙ በጎ ተግባራት የሚከናወኑባት ቢሆንም አዎንታዊ ሁነቶች የተለየ ስሜት ቀስቃሽነት፣ እንግዳነት ወይም አሀዛዊ ግዝፈትና ተጽዕኖ ከሌለባቸው የዘጋቢዎችን ትኩረት አይስቡም፡፡ የሰዎችን ሞትና ጉዳት የማስቀደም መርህ ለብቻው ተነጥሎ ሲታይ ትክክል ነው፡፡ በሰዎች ህይወት ላይ የሚደርስ አደጋና ጉዳት ቅድሚያ ማግኘቱ ተገቢነት አለው፡፡

ሆኖም ከመላው ዓለም የሚሰበሰቡ የግጭት፣ የሁከት፣ የነውጥ፣ የጦርነት፣ የውድመት፣ የሞት፣ የሥቃይ፣ የመፈናቀልና የመሰደድ ዘገባዎች መደበኛ የመገናኛ ብዙሀን የዜና አቅርቦት ዋነኛ ይዘት መሆናቸው በሰዎች እሳቤና ማህበራዊ ሥነልቦና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡ ዓለም የጦርነት አውድማ ነች፤ የሰዎችም እጣ ፈንታ ስቃይ፣ መከራና ሞት ነው የሚል ጨለምተኛ አተያይ እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል፡፡ በየእለቱ ዜና የሰዎች ሞትና ሥቃይ ሲቀርብ የመገናኛ ብዙሀን ተደራስያንን ስለ ሰዎች ሥቃይና ሰቆቃ የማዘንና የመደንገጥ ስሜት ቀስ በቀስ እያዳከመው ይሄዳል፡፡ የህዘንና ርህራሄ ስሜት አልባነት፣ ስልቹነትና ግዴለሽነት ይፈጥራል፡፡

መገናኛ ብዙሀን የሰዎችን ስሜቶች በሚያወኩ ነውጠኛ ክስተቶች ላይ ትኩረታቸውን ከመገደብ ይልቅ የግጭቶችን መሰረታዊ ምክንያቶች በጥልቀት በመመርመር የህዝብንና ባለድርሻ አካላትን የመገንዘብና መፍትሄ ፈልጎ የማግኘት አቅም ለማሳደግ የሚያደርጉት ጥረት አዎንታዊ አስተዋጽኦዋቸውን ይበልጥ እንደሚያጎለብተው ይታመናል፡፡ ይህም ሚና በግጭት ወቅት የሚናፈሱ ሀሰተኛ መረጃዎችን ማጋለጥን፣ የተዛቡ እሳቤዎችን ማረቅንና የማህበረሰብን እውቀት በማበልጸግ የሰላማዊ መፍትሄዎችን እድል ማጎልበትን ያካትታል፡፡[1]

## ተግባራት

- በጦርነትና በግጭት ዘገባዎች ውስጥ የሰዎችን ሞትና ሥቃይ ተደራስያንን በሚያስቆጣና የበቀል ስሜት በሚቀሰቅስ ተውኔታዊ አቀራረብ አትዘግቡ፡፡
- በዓለም ውስጥ ግጭትና ጦርነት ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ በሰላም አብሮ የመኖር፣ በጋራ የመልማትና የማደግ ተስፋውን የሚያሳዩ በጎ ተግባራት መኖራቸውን ለሚያሳዩ ሁነቶችም ሰፊ ሥፍራ ስጡ፡፡
- መገናኛ ብዙሀን ዜና ሲዘግቡ መልስ የሚፈልጉላቸው ምን? ማን? የት? መቼ? እንዴት? እና ለምን? የሚሉ ስድስት መሰረታዊ ጥያቄዎች አሏቸው፡፡ ይህ የነባሩ ሙያዊ ጋዜጠኝነት የመረጃ ማሰባሰቢያና ዜና መዘገቢያ ማእቀፍ ነው፡፡ ሆኖም ግጭትን ከመፍታትና የማህበረሰብን ሰላም ከመገንባት አንጻር ይበልጥ እንዲያገለግል አንድ ተጨማሪ ጥያቄ ሊካተት ይገባል የሚል ምክረሀሳብ አለ፡፡ ይህም በግጭት ዘገባ ውስጥ ሁሉ «መፍትሄውስ?» የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ ነው፡፡ ስለዚህ ስለ ግጭት ስትዘግቡ የግጭቱን መንስዔ ሂደትና ውጤት ከሚመለከቱ ጥያቄዎች በተጨማሪ «መፍትሄውስ?» ብላችሁ ጠይቁ፡፡
- «መፍትሄውስ?» የሚለው ጥያቄ የሚቀርበው በግጭቱ ውስጥ ላሉ ተፎካካሪ ወገኖች፣ ተወካዮች፣ በግጭቱ ምክንያት ተጎጂ ለሆኑ የማህበረሰቡ አባላትና ባለድርሻዎች ነው፡፡ የጥያቄው ዋና ዓላማ

[1] Essia, Uwem (2020). Media for Peacebuilding Guidebook. Global Forum for the Defence of the Less Privileged: Cameroun.

የመፍትሄ ሀሳቦች ከባለጉዳዮቹና ማህበረሰቡ እንዲመነጩ ማድረግ ነው፡፡

- ግጭቶችን ወደ መግባባት ለመለወጥ የሚሰሩ መገናኛ ብዙሀን ግጭቶችንና ልዩነቶችን ሳይዘነጉ ተፎካካሪ ወገኖችን ከሚለያዩዋቸው ጉዳዮች በላይ በሚያስማሟቸው ነጥቦች ላይ ያተኩራሉ፡፡ ስለዚህ የግጭት ዘገባ ስትዘግቡ የምታነሷቸው ጥያቄዎች ልዩነቶችን ከጋራ ፍላጎቶች ጋር የሚያስተሳስሩ ይሁኑ፡፡

## መርህ 2
## ስለ ግጭት ባህሪ እውቀትህ አሳውቁ

### አጭር መግለጫ

ግጭት አይቀሬ ነው፡፡ በተፈጥሮና በማህበረሰብ ውስጥ ባሉ ልዩነቶች ምክንያት ሊከሰት ይችላል፡፡ አለመግባባት በግለሰቦች፣ በቤተሰብ አባላት፣ በቡድኖች፣ በማህበረሰብ፣ በተቋማትና በሀገሮች መካከል የሚኖር ክስተት ነው፡፡[2]

በሰዎች መካከል ያሉ ልዩነቶች የግጭት መነሻ የመሆን አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡ ማንም ግጭት እንዳይኖር የማድረግ አቅም የለውም፤ ምክንያቱም ግጭት ከማህበረሰብ የማይነጠሉ ባህሪያት አንዱ በመሆኑ ነው፡፡

ግጭቶች ተጨባጭና ግልጽ ሆነው ሊዘረዘሩ ከሚችሉ እንደ ጭቆና፣ የኑሮ ዋስትና ማጣት፣ መገለል፣ የሙብት መነፈግ ወይም የእኩልነት፣ የፍትህና የነጻነት እጦት ባሉ ምክንያቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ እነዚህ እጦቶች በደል የሚሰማውን ወገን ምሬቱን እንዲገልጽ፣ እንዲቃወምና እንዲያምጽ ሊያደርጉት ይችላሉ፡፡

ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ሀብቶችን ማግኘት ከባድ መሆኑ በማህበረሰቦችና በሰዎች መካከል ላለው ውድድርና ሽሚያ መበርታትና ለግጭቶች መፈጠር ዋና ምክንያት ነው፡፡ የኑሮ ዋስትናን ለማረጋገጥና ስኬታማ ለመሆን መፎካከር፣ መወዳደርና መታገል ግዴታ ቢሆንም የመጥፋትና የህልውና ስጋት ሰዎችን ወደ ግጭት እንዲገቡ ያደርጋቸዋል፡፡ ሰዎች ከሰዎች ጋር ሲኖሩ የመሰሎቻቸውንና የራሳቸውን ኑሮ እንደተደጋጋፊ ከመቁጠር ይልቅ እንደ አጥፊና ጠፊ ግንኙነት ማየታቸው ጥላቻንና ኃይል የመጠቀም ፍላጎት ግጭቶችን ወደ ነውጥ እንዲሸጋገሩ አድርጓቸዋል፡፡

ግጭት በርዕዮተ ዓለምና በእሳቤ ካለመግባባትም ሊመነጭ ይችላል፡፡ አንድ ወገን እንደ ባህላዊ፣ እምነታዊ፣ ፖለቲካዊና ርዕተዓለማዊ እሴቱ የሚቆጥረውንና የሚወደውን ምልክትና ትርጉም ሌላው ወገን በጥላቻ የሚያየውና የሚቃወመው ከሆነ ግጭት ሊፈጥር ይችላል፡፡ የአስተያየትና የአተረጓጎም ግጭቶች ረቂቅ ከሆኑ የግጭት ምክንያቶች መካከል የሚካተቱ ናቸው፡፡[3]

ግጭት ከማህበረሰብ ህልውና የማይነጠልና የማይቀር ቢሆንም ወደ ነውጥ፣ ሁከትና ጦርነት እንዳይሸጋገር ማድረግ ግን ይቻላል፡፡ ግጭት የማይቀር፣ ጦርነት ግን ምርጫ ነው፡፡ አንድ ግጭት ከጅምሩ መፍትሄ እንዲያገኝ ሰዎች ለመተባበር ከቆረጡ ወደ ቁጣ፣ ነውጥና ጦርነት ከመሸጋገሩ በፊት መፍትሄ ሊያገኙለት ይችላሉ፡፡ ግጭቶች አለመግባባት ከመሆን አልፈው በግልጽ ወደሚታይ ሁከት፣ ብጥብጥና ነውጥ የሚሸጋገሩት ተፎካካሪ ወገኖች መግባባት ከማይችሉበት ደረጃ መድረሳቸውን ማመን ሲጀምሩ ነው፡፡[4]

---

[2] ሕዝቅያስ አሰፋ (2011)፤ የሰላምና እርቅ ትርጉምና መንገዶች፡ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እድገትና ከተፈጥሮ ጋር ባሉን ግንኙነቶች ላይ ያሏቸው አንድምታዎች፡፡ አዲስ አበባ፡፡

[3] Essia, Uwem (2020). Media for Peacebuilding Guidebook. Global Forum for the Defence of the Less Privileged: Cameroun.

[4] Çiftcioğlu, Vasvi (2017). Peace Journalism: A Practical Handbook for Journalists in Cyprus. Naci Talat Vakfı and IKME: Nicosia.

## ተግባራት

- ግጭቶች የተከሰቱባቸውን ሁነቶች ለመዘገብ የምትሰጡትን ትኩረት ያህል ምክንያታቸውንና እድገታቸውን የሚመለከቱ በቂ ጥያቄዎች ጠይቁ፡፡ የግጭቱ ምክንያት ምንድነው? የተጋጩት እነማን ናቸው? ተጋጪዎቹ ስለ ግጭቱ መነሻ የሚያቀርቧቸው ምክንያቶች ተመሳሳይ ናቸው ወይ? ልዩነቶቻቸው ምንድናቸው? ከተጋጪዎቹ ጀርባ ግጭቱን የሚያበረታቱ አካላት ሊኖሩ ይችላሉ ወይ? የሚሉትንና ሌሎች ክስተቱን ይበልጥ ለመረዳት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን ጠይቁ፡፡

- ተፎካካሪ ወገኖች በማህበረሰቦች ውስጥ የሚከሰቱ ግጭቶችን በሚመለከት ያላቸውን ግንዛቤ እንዲገልጹ የሚያበረታቱ ጥያቄዎችን ጠይቁ፡፡

- የግጭት መፍትሄ በተለያየ መልክ ከተፎካካሪ ወገኖችና ባለድርሻዎች የግጭት ግንዛቤና ብየና ጋር  የሚያያዝ በመሆኑ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የግንዛቤ ልዩነትን ለማጥበብ የሚረዱና የጋራ አስተያየቶችን በሚያበረታቱ ነጥቦች ላይ አተኩሩ፡፡

- በግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች አለመግባባታቸውን ለመፍታት ወደ ውይይት፣ ድርድር፣ የህግ አማራጮችና ሌሎች ሰላማዊ መንገዶችን ስለመሞከር አስፈላጊነት እንዲናገሩ የሚያበረታቱ ጥያቄዎችን ጠይቁ፡፡

- በግጭት ወቅት በቀጥታ ተሳታፊ ከሚሆኑ ወገኖች ውጭ ጠቅላላው ማህበረሰብም ጉዳዩ እንደሚመለከተው በመገንዘብ የህዝብ አስተያየትን የዘገባዎቻችሁ አካል አድርጉ፡፡

- ስለ ግጭቱ የመገናኛ ብዙሀን ተደራስያን ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያሳዩና እነሱም የመፍትሄ ሀሳባቸውን እንዲያቀርቡ እድል ስጧቸው፡፡

- ግጭት ወይም አለመግባባት ከሰዎች አቅም በላይ የሆነና ተስፋ አስቆራጭ ክስተት አለመሆኑን፤ ይልቁንም ሰዎች ማህበረሰባዊ ህይወታቸውን የሙተጋገዝና የትብብር ለማድረግ ወደሚያስችላቸው ጉዞ የሚገቡበት የመጀመሪያ እርምጃ ሊሆን እንደሚችል የሚያሳዩ የማህበረሰብ መሪዎችና የባለሙያዎች ውይይቶችን አበረታቱ፡፡

## መርህ 3
## ግጭት በራሱ መጥፎም ጥሩም አለመሆኑን ተረዱ

### አጭር መግለጫ

ግጭት በራሱ መጥፎም ጥሩም አይደለም፡፡ ግጭትን ጥሩና መጥፎ የሚያደርገው አያያዙ ነው፡፡ ሰዎች በመካከላቸው የሚፈጠርን ግጭት በመግባባትና በሰላም መፍታት ከቻሉ የሰዎችን መፈናቀልና ሞት፣ የአካልና የአእምሮ ጉዳት፣ የንብረት ውድመትና ጥፋት ያስቀራሉ፡፡ በሰላም አብሮ በመኖር የጋራ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ በጋራ ያተርፋሉ፡፡ ተባብረው ለመልማት የሚያስችላቸውን የተሻለ የግንኙነት መስመር ያሰምራሉ፡፡ ግጭትን በሰላም መፍታት ፈታኝ ቢሆንም ስኬቱ የሰዎችን ፈተና የማሸነፍና ወደ ስኬት የመጓዝ አቅም ይመሰክራል፡፡ ወደ ሰላማዊ መፍትሄ ማምራት ካልቻሉ ግን በጋራ ይጠፋፋሉ፡፡ የግጭትን ባህሪ የሚወስነው የሰዎች ከመፍትሄ የመድረስ አቅምና ፈቃድ ነው፡፡ [5]

ግጭቶች ማህበረሰብ መለወጥና መሻሻል እንደሚያስፈልገው የሚጠቁሙ ምልክቶች ናቸው፡፡ በአዲስ ፍልስፍናና አስተሳሰብ፣ በተለየ ፈጠራና የእድገት አቅጣጫ የሚታገዝ ለውጥ እንደሚያስፈልግ ይጠቁማሉ፡፡ ግጭቶች ተወሳስበው ወደ ነውጥና ሁከት ከመሸጋገራቸው በፊት ትኩረት ከተሰጣቸውና ተገቢ እርምጃዎች ከተወሰዱ ማህበረሰብን ወደ አዎንታዊ ለውጥና እድገት የማሸጋገር ሚና ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ግጭቶችን እንደ መልካም አጋጣሚ መቁጠር ይቻላል፡፡

## ተግባራት

- በግጭት ዘገባዎቻችሁ አለመግባባቶችን እንደ አስደንጋጭ ክስተቶች አታቅርቡ፡፡
- ግጭቶች የማይቀሩ የማህበራዊ እውነታ አካል መሆናቸውንና መፍትሄያቸውም ከሰዎች አቅም በላይ እንዳልሆነ ሊያሳዩ የሚችሉ ጥያቄዎችን ጠይቁ፡፡
- በማህበረሰቡ ተሞክሮ ውስጥ የታወቁ ተዛማጅ የግጭት አጋጣሚዎች የተፈቱባቸውን መንገዶች የሚያሳዩ የዳራ መረጃዎች በዘገባዎቻችሁ ውስጥ አካትቱ፡፡
- የታወቁ የግጭት መፍቻ ባህላዊ ተሞክሮዎችን የሚመለከቱ ዘገባዎችን በመስራት ወቅታዊ ግጭቶች በነባር የግጭት መፍቻ ተሞክሮዎች ሊታገዙ የሚችሉባቸውን እድሎች ማሳየት የሚችሉ ምንጮችን ጠይቁ፡፡
- የግጭቶች መቀስቀስ የህግና የፖሊሲ ማሻሻያ ጥያቄ ወይም የማህበረሰባዊ ለውጥ አንድምታ ይኖረው እንደሆነ ሊያስረዱ የሚችሉ ምንጮችን አወያዩ፡፡
- ግጭቶችን በጋራ መፍትሄ ወደ መልካም አጋጣሚ መቀየር የሚቻልባቸውን አማራጮች ለማሳየት ሞክሩ፡፡

---

5 Bloh, Oscar. 2010. Strategic Communication for Peacebuilding a training guide How to use strategic communication on development objectives as a tool for peacebuilding. Search for Common Ground/Radio Peacebuilding Africa, New York.

## መርህ 4
## ግጭት ሂደት መሆኑን ተገንዘቡ

### አጭር መግለጫ

ግጭት በማህበረሰብ ውስጥ ባሉ ልዩነቶች ላይ ተመስርቶ በሂደት ሊያድግ የሚችል ክስተት ነው፡፡ ስለ ግጭት በመዘገብ ማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲኖረው የማድረግ ተግባርና ለሰላማዊ መፍትሄ አስተዋጽኦ የማበርከት ድርሻ በአንድ ሰሞን ዘገባ ብቻ አይጠናቀቅም፡፡ የጋራ መግባባት መፍጠር ሂደት ነው፡፡ ተከታታይ ጥረት የሚጠይቅና ደረጃ በደረጃ የሚከወን ተግባር ነው፡፡

ግጭቶችን በመፍታት ሂደት ውስጥ ባለድርሻዎች በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጽሟቸው ተግባራት የጋራ መግባባትን የሚያበረታቱ ብቻ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ሂደቱን ወደ ኋላ የሚመልሱ ድርጊቶችም ይኖራሉ፡፡ ውጥረትና ስጋት ሊጨምር ይችላል፡፡ የክስተቶቹ ዳራዎች (ተያያዥ የኋላ ሁነቶች) እየበዙ ይሄዳሉ፡፡
መገናኛ ብዙሀንም ስለ አንድ አዲስና ወቅታዊ ሁነት ሲዘግቡ የዳራ መረጃ ማካተት ይኖርባቸዋል፡፡ የዳራ መረጃ ይዘቶች የአንድን ግጭት መነሻና እድገት፣ የግጭቱን ተጽዕኖ፣ ግጭቱን ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶችንና የተገኙ ውጤቶችን የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም የግጭትን ሂደት ተደራስያን እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል፡፡ ግጭቱን ወደ መፍትሄ በሚያራምዱትና ወደ ኋላ በሚመልሱት ክስተቶች ላይ ተከታታይ ትንታኔዎችን ማቅረብ በሂደቱ ውስጥ የሚታዩትን ተቃርኖዎች ለመረዳት ያስችላል፡፡[6]

## ተግባራት

- ግጭት የራሱ ምክንያት፣ የመነሻ ሁኔታና ሂደት ስለሚኖረው ስለ አንድ የግጭት ክስተት ስትዘግቡ የሁነቱን ሙሉ ስዕል ለማሳየት የዳራ መረጃ ተጠቀሙ፡፡

- በክስተቱ ውስጥ ተዋናይ የሆኑትን አካላት ማንነት በዳራ መረጃ በመጠቀም ግለጹ፡፡

- በግጭቱ ውስጥ በየጊዜው የሚታዩ ሁነቶች (ውዝግቦች፣ ሰዶ ማሳደዶች፣ ውሳኔዎች፣ የተቃውሞ ሰልፎች፣ ረብሻዎች፣ ጥቃቶች፣ የፍርድ ቤት ችሎቶች፣ ድርድሮች፣ የእርቅ ውይይቶች) በምክንያትና ውጤት ዝምድናቸው መሰረት በዘገባዎቻችሁ ውስጥ እንዲገለጹ አድርጉ፡፡

- የመገናኛ ብዙሀን መልእክቶች የተደራሲዎቻቸውን አስተያየት አዎንታዊ የማድረግ ተጽዕኖ ሊኖራቸው የሚችል ከሆነ ለውጡ ጊዜ የሚወስድ መሆኑን በመገንዘብ ዘገባዎቻችሁን ተከታታይና ተያያዥ አድርጉ፡፡

[6] Essia, Uwem (2020). Media for Peacebuilding Guidebook. Global Forum for the Defence of the Less Privileged: Cameroun.

## መርህ 5
## ለቀላል ማህበረሰባዊ ግጭቶች ትኩረት ስጡ

### አጭር መግለጫ

ቀላል የሚመስሉና ጎልተው ያልወጡ ግጭቶች የመገናኛ ብዙሀንን ትኩረት የመሳብ አቅማቸው አነስተኛ ነው፡፡ መገናኛ ብዙሀን ከፍ ያለ ትኩረት የሚሰጡት ተጽዕኗቸው ለሚታይ ግጭቶች ነው፡፡ አደጋ ደርሶ የሰዎች ህይወት ሲያልፍና ጉዳት ሲደርስ ለመዘገብ ይሽቀዳደማሉ፡፡ ገና ከግጭቶቹ መነሻ ታይተው የነበሩና ያልዘገቧቸውን ቀላል አለመግባባቶች ነውጠኛና አውዳሚ ሁከቶች ሲቀሰቀሱ የዘገባቸው ዳራ አድርገው ያቀርቧቸዋል፡፡ ይህ ዝንባሌ መገናኛ ብዙሀን ግጭቶችን ከመፍታት አንጻር የሚያበረክቱትን አዎንታዊ አስተዋጽኦ ዝቅ ያደርገዋል፡፡

መገናኛ ብዙሀን አደጋ ሲከሰት ከመጮህ ይልቅ አደጋ ከመድረሱ በፊት የግጭት ዘሮች ገና በማጎንቆል ደረጃ ላይ እያሉ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሚና መጫወት ይገባቸዋል፡፡ አስጠንቃቂነት ከመገናኛ ብዙሀን ኃላፊነት አንዱ ነው፡፡ በቅድሚያ የማስጠንቀቅ ሚና ገና በእንጭጭ ደረጃ ላይ ያሉና በሀሳብ ያለመግባባት ላይ የተወሰኑ ግጭቶችን በመተንተንና ምንነታቸውን በማብራራት መግባባት የሚቻልበትንና መፍትሄ የሚገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው፡፡ ይህም የአንድ ግጭት ባለድርሻዎች ችግሮቻቸውን ተረድተው ተግባራዊ እርምጃ እንዲወስዱ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡[7]

የማህበረሰቡን ችግሮች የመፍታት አዎንታዊ ሚና ያላቸው መገናኛ ብዙሀን ግጭቶች ወደ ነውጥ ደረጃ እስኪያድጉ አይጠብቁም፡፡ ከመነሻቸው ጀምሮ ተከታታይ መፍትሄ ተኮር ዘገባዎችን ይሰሩባቸዋል፡፡ የምክንያትና የውጤት ትስስሮችን በማሳየት የተደራሲዎቻቸውን ግንዛቤ ያሳድጋሉ፡፡ አሉታዊ አዝማሚያዎችን በመከታተል ማህበረሰቡ የከፉ ችግሮች ከመከሰታቸው በፊት መፍትሄ እንዲያበጅላቸው ጥረት ያደረጋሉ፡፡

የግጭቶች መነሻ ችግሮችን ከማለዳው ለመፍታት ጥረት ካልተደረገ ልዩነቶች እያደጉ ውስብስብ ባህሪ ይይዛሉ፡፡ በተወዛጋቢ ወገኖች መካካል የበረታ የጥላቻ ስሜትና አሉታዊ የጠባይ ለውጦች ከመፍጠራቸው በፊት ግጭቶችን መፍታት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ የጠባይ ለውጥ ተከስቶ ስሜታዊ ነውጦች ከተፈጠሩ በኋላ ሰላማዊ መፍትሄ ማግኘት ከባድና አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ተወዛጋቢ ወገኖች በአሉታዊ ስሜት ጫና ስር ከሆኑ በኋላ ከመነሻው ግጭቶቹ ስለመኖራቸው ጥርጣሬ የነበራቸው ወገኖች ጠላትነት እንዳለ ከማመን አልፈው ስለመኖሩ እርግጠኛ መሆን ስለሚጀምሩ ግጭቶችን በዚህ ደረጃ መፍታት ከባድ ፈተና ይሆናል፡፡

የዓለም የግጭት ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት አብዛኛዎቹ በሰዎች ላይ ከፍተኛ የህይወት ጥፋትና ውድመት ያደረሱ ነውጦች የተጀመሩት በቀላል አለመግባባት፣ በውዝግብና ሙግት፣ በውግዘትና ማስጠንቀቂያ፣ አብሮ መስራትንና ግንኙነትን በማቋረጥ፣ በማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን ትችቶችና የተቃውሞ ሰልፎች፣ በእምቢታና በአድማዎች ነው፡፡ እነዚህ ምልክቶች እምቅ የነበረ ግጭት አድጎ ገሀድ መውጣቱን ይጠቁማሉ፡፡ መፍትሄ ይሻሉ፡፡ ወደ ሰላማዊ መፍትሄ የሚወስዱ እርምጃዎችን ከመነሻው መፈለግ ግጭቶች ወደ አውዳሚ ነውጥ እንዳይሸጋገሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ያለመግባባቶችንና የግጭቶችን ምክንያት በጊዜ ተገንዝቦ ለመፍታት መሞከር ውስብስብ ሁከቶችን፣ ነውጦችንና ጦርነቶችን ለማስቀረት አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡[8]

---

[7] Essia, Uwem (2020). Media for Peacebuilding Guidebook. Global Forum for the Defence of the Less Privileged: Cameroun.

[8] Çiftcioğlu, Vasvi (2017). Peace Journalism: A Practical Handbook for Journalists in Cyprus. Naci Talat Vakfı and IKME: Nicosia.

## ተግባራት

- ከሀብት አጠቃቀም፣ ከአስተዳደራዊ መብቶች፣ ከልማት ተጠቃሚነትና ከባህል እውቅና ጥያቄዎች ጋር ለተያያዙ ማህበረሰባዊ ቅሬታዎች ትኩረት በመስጠት ዘግቡ፡፡

- በማህበረሰቦች መካከል ነውጠኛ ግጭቶችን ሊቀሰቅሱ ለሚችሉ አነስተኛ ህገወጥ እንቅስቃሴዎች፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችና ጥቃቶች ትኩረት በመስጠት ዘግቡ፡፡ ችግሮቹ እንዳይስፋፉ የማድረግ ድርሻ ያላቸውን የማህበረሰብ፣ ህግና የአስተዳደር አካላት ጠይቁ፡፡

- በግጭቱ ውስጥ የተገፉ፣ የተጨቆኑና ፍትህ ያጡ ወገኖች ድምጽ በመሆን የአንድ ማህበረሰብ በደል የሁከትና ነውጥ ምክንያት ከመሆኑ በፊት ምላሽ ማግኘት ለሚያስችሉ ዘገባዎችና ውይይቶች ትኩረት ስጡ፡፡

- ለፖለቲካዊ አለመግባባት ምክንያቶች ሊሆኑ በሚችሉ የህግና የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የውይይት መድረኮችን አመቻቹ፡፡

- የተለያዩ ተፎካካሪ ሀሳቦችን የሚያራምዱ ወገኖችን በማሳተፍ ልዩነቶቻቸውንና ተመሳሳይ አቋሞቻቸውን እንዲያብራሩ የሚጋብዙ ጥያቄዎችን ጠይቁ፡፡ ስለ ችግሮቻቸው የመፍትሄ ሀሳብ እንዲያቀርቡ አበረታቱ፡፡

- አለመግባባት የሚከሰተው የማህበረሰብ አባላት የጋራ መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን በምልዓት መግለጽ ወይም መበየን ሲሳናቸውና በብያኔዎቻቸውም ላይ ከጋራ መግባባት መድረስ ሲያቅታቸው ስለሆነ በዘገባዎቻችሁ ውስጥ የጋራ መብቶችና ጥቅሞች ትርጓሜ ጎልቶ እንዲወጣ አበረታቱ፡፡

- የግጭቶች መንስዔዎች በጥልቀት እንዲታወቁ ከላይ ከሚታዩ ገጽታዎቻቸው ባሻገር መሰረታዊ ምክንያቶችን ለማሳየት የሚያስችሉ ምርመራዎችን አድርጉ፡፡ ባለድርሻዎችን፣ ከግጭቱ ጋር ተያያዥነት ባላቸው አርዕስት ላይ ባለሙያዎችንና ተመራማሪዎችን ጠይቁ፡፡

- የተከሰቱ ግጭቶች ከመነሻቸው ካልተፈቱ ወዴት ሊያመሩ እንደሚችሉ የሚጠቁሙ ማብራሪያዎችና የመፍትሄ እርምጃዎች ውይይት እንዲደረግባቸው አበረታቱ፡፡

## መርህ 6
## ስለ ግጭት ስትዘግቡ ነጻና ሚዛናዊ ሁኑ

### አጭር መግለጫ

ግጭት ከተግባቦት ጋር በማይነጣጠል ሁኔታ የተዋሀደ መሆኑ መገናኛ ብዙሀን በግጭት አፈታት ሂደት ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና ወሳኝ ያደርገዋል፡፡ አንድ ግጭት ተጸንሶ፣ ተወልዶ፣ አድጎ በገሀድ መታየት በሚችልበት ደረጃ የሚከሰተው በተግባቦት መዛባት ወይም ባለመግባባት መልክ ስለሆነ መገናኛ ብዙሀንን ከጉዳዩ ባለቤቶች አንዱ ያደርጋቸዋል፡፡

በተለያዩ ተወዛጋቢ ወገኖች መካከል የጋራ መግባባት እንዲኖር የሚያስችል ወይይት በማሳለጥ ግጭቶች እንዲፈቱ ለማድረግ ወይም ወደ ነውጥ መሸጋገራቸውን በመግታት ረገድ የመገናኛ ብዙሀን ሚና ምትክ አይገኝለትም፡፡ ሆኖም የሚናቸው አዎንታዊነት የሚወሰነው በሙያዊ ነጻነትና በሚዛናዊነት ላይ ነው፡፡[9]

በዘገባዎቻቸው ውስጥ ለየትኛውም ቡድን ዓላማ ሳይሆን ለህዝብ በሰላም አብሮ የመኖር ፍላጎት ቅድሚያ ሊሰጡ ይገባል፡፡ የህዝብ በሰላም አብሮ መኖር ከፖለቲካ ቡድኖችና ከፖለቲካ መሪዎች ፍላጎት በላይ መሆኑን ማሳየት አለባቸው፡፡ የሙያ ነጻነትና ሚዛናዊነት መገናኛ ብዙሀን በግጭት ውስጥ ድርሻ ካለው ከየትኛውም ቡድን ጋር እንዳይወግኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በወገንተኛነት የአንደኛውን ሚና በጎ፣ የሌላውን ደግሞ እኩይ በማለት አይፈርጁም፡፡ «እኛ» እና «እነሱ» የሚሉ ከፋፋይ ምድቦችን አይፈጥሩም፡፡ ሚናቸው ማቀራረብ እንጂ ልዩነትን ማስፋት አይሆንም፡፡

ስለ ግጭት ሀላፊነት የተሞላበት ሙያዊ ዘገባ የማቅረብ ሚናቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ሁሌም ከወገንተኝነት ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ከየትኛውም ወገን ተጽዕኖ ነጻ የሆኑ ጋዜጠኞች የማህበረሰብን ፍላጎት የሚወክሉ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፡፡ የሙያ ነጻነት የዘገባ ሚዛናዊነት እንዲኖር የሚያስፈልግ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ ሚዛናዊነት ኃላፊነት የተሞላበት ሙያዊ የግጭት ዘገባ ለማቅረብ የሚያስችል ወሳኝ እሴት ነው፡፡ መገናኛ ብዙሀን ማህበረሰቡን በትክክል እንዲያገለግሉ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ በማህበረሰባቸው እንዲታመኑ ያደርጋቸዋል፡፡ መታመናቸው ተቀባይነት ያስገኝላቸዋል፡፡ የተጽዕኖ ፈጣሪነትና የአዎንታዊ ለውጥ አራማጅነት ድርሻቸውን ያሰፋዋል፡፡[10]

### ተግባራት

- በመረጃ ምንጮቻችሁና በተደራሲያን ዘንድ ተዓማኒ እንድትሆኑ ዜና ለመዘገብ የምትጠይቋቸው ጥያቄዎች ከወገንተኝነትና ከአድሏዊነት ነጻ ይሁኑ፡፡

- በግጭት ወቅት ተጎጂ ስለሆኑ ማህበረሰቦች ስትዘግቡ የአንደኛውን ወገን መከራና ስቃይ በማሳየት አትወሰኑ፡፡ ሌላውም ወገን ስለደረሰበት ተመሳሳይ ፈተና ዘግቡ፡፡

- ጥያቄዎቻችሁ የተለያዩ ተወዛጋቢ ወገኖችን እይታዎች የሚወክሉ መሆናቸውን እርግጠኛ ሁኑ፡፡

- የዘገባዎቻችሁ ይዘት በግጭት ውስጥ ያሉ ተዋንያን አንዱ ስለሌላው ያለውን የተዛባ አመለካከት

---

[9] Howard, Ross. (2008). Conflict Sensitive Journalism: A Handbook. (Special Edition Kenya). International Media Support.

[10] Essia, Uwem (2020). Media for Peacebuilding Guidebook. Global Forum for the Defence of the Less Privileged: Cameroun

ለማስተካከል የሚያግዝ ይሁን፡፡ ሁለቱም ወገኖች «እኛ እንዲህ እንጂ እንደዚያ አይደለንም» እንዲሉ እድል ስጧቸው፡፡

- የትኛውንም የግጭት ወገን በዘገባ ውስጥ ስትጠቅሱ መደበኛ ስሙን ተጠቀሙ፡፡

- የግጭት ዘገባ መረጃ ማግኘት ከባድ ቢሆንም የደረሱ ጥፋቶችን በሚመለከት በተወዛጋቢዎች መካከል መወነጃጀልና መካካድ ሲያጋጥም በሌሎች አማራጭ ምንጮች መረጃ ለማጣራት ጥረት አድርጉ፡፡

- ስለ አንድ የግጭት ጉዳይ ስትዘግቡ የአንድ ወገን መረጃ ብቻ አግኝታችሁ የሌላውን ወገን መረጃ ማግኘት ካልቻላችሁ በዜናችሁ ውስጥ ማሚያ መረጃ ለማካተት ያደረጋችሁትን ያልተሳካ ጥረት አስታውቁ፡፡

# መርህ 7
# የግጭት ዘገባዎቻችሁን አካታች አድርጉ

## አጭር መግለጫ

ግጭት ዘርፈ ብዙና የልዩ ልዩ ባለድርሻዎች ጉዳይ ነው፡፡ በቀጥታ ተጋጭ ከሆኑት ወገኖች ሌላ ግጭቱ የሚመለከታቸው የማህበረሰብ አካላት አሉ፡፡ ይህም መገናኛ ብዙሀን ስለ ግጭት ሲዘግቡ ጉዳዩን የሁለት ቡድኖች ችግር ብቻ አድርገው ከማቅረብ መቆጠብ እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡ በዘገባዎቻቸው ውስጥ የአካታችነት መርሆዎችን እንዲከተሉ ያስገድዳቸዋል፡፡ የአካታችነት መርሆ በየዘገባ ጉዳዮች ውስጥ የሚመለከታቸው ባለድርሻዎች የመረጃ ምንጭ ሆነው መግባታቸውን ማረጋገጥ የግድ ይላል፡፡ [11]

ግጭቶች የሚቀሰቀሱት ቢያንስ በሁለት ቡድኖች መካከል ቢሆንም ክስተቱ የሚመለከታቸው ብዙ ወገኖች ይኖራሉ፡፡ በግጭት ምክንያት ኑሯቸው በልዩ ልዩ ምክንያት የሚናጋባቸው ማህበረሰቦች መኖራቸው አይቀርም፡፡ ስራቸውን የሚያጡ፣ የሚፈናቀሉ፣ የስራ እቅዳቸውን የሚሰርዙ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የሚያስተላልፉ ግለሰቦች፣ ማህበረሰቦችና ድርጅቶች ይኖራሉ፡፡ ተቋማት ስራቸውን ሊያቆሙና ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል፡፡ እነዚህ ሁሉ አንድን ግጭት በሚመለከት ሊሰማና ሊታወቅ የሚገባው የየራሳቸው አስተያየትና ትርጓሜ ሊኖራቸው ይችላል፡፡[12]

አካታችነት ተጻራሪ ሀሳቦች ከአማካኝ ሀሳቦች ጋር በአግባቡ እንዲስተናገዱ ያደርጋል፡፡ ተወዛጋቢ አስተያየቶችን ከአማካኝ ሀሳቦች ጋር ማስተናገድ ግጭትን ለመረዳትና ለሰላማዊ መፍትሄ አስተዋጽኦ ለማበርከት ይረዳል፡፡ በመፍትሄ ተኮር የግጭት ዘገባ ውስጥ ችግሮችን ከመፍትሄ ሀሳቦች ጋር ለማቅረብ ያግዛል፡፡

## ተግባራት

- ግጭቶችን በሚመለከት ስትዘግቡ ከመሪዎች በስተጀርባ ያሉትን ልዩ ልዩ ወገኖች ፍላጎትና አስተያየት አትርሱ፡፡
- ስለ አንድ ግጭት የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር የሁሉም ባለድርሻዎች ድምጾች የመደመጥ እድል እንዲያገኙ አድርጉ፡፡
- የመፍትሄ ሀሳቦች ከሁሉም ባለድርሻዎች እንዲመነጩ አበረታቱ፡፡
- ከግጭቶች የሚያተርፉና ሰላማዊ መፍትሄ እንዳይገኝ እንቅፋት የሚፈጥሩ ቡድኖች ካሉ ፍላጎታቸውን የሚያጋልጡ ዘገባዎችን ስሩ፡፡

[11] Jenkins, Tony and Betty A. Reardon. "Gender and peace: Towards a gender-inclusive, holistic perspective" in Webel, Charles and Johan Galtung(eds.). 2007. Handbook of Peace and Conflict Studies. Routledge: New York.
[12] Howard, Ross. (2008). Conflict Sensitive Journalism: A Handbook. (Special Edition Kenya). International Media Support.

## መርህ 8
## ከግጭት ዘገባ ምሉዕነት ጋር ሙያዊ ኀላፊነትን አስቡ

### አጭር መግለጫ

የግጭት ዘገባ የተሟላ መሆን አለበት፡፡ ጋዜጠኞች ግጭትን አቃልለው፣ መቅረብ የሚገባውን መረጃ አጉድለው ወይም ቀንሰው መዘገብ አይጠበቅባቸውም፡፡ በግጭቱ ውስጥ ያሉ ባለድርሻዎች፣ የቦታና ጊዜ መረጃ ሁሉ በዘገባ ውስጥ መካተት ይገባዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዜና ውስጥ ያሉ አንዳንድ ዝርዝሮች ግጭትን የሚያስፋፉ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ግለሰቦችን፣ ተቋማትን፣ የአንድ ማህበረሰብ አባላትንና ሀገርን ሊጎዳ የሚችል ባህሪ ካላቸው አጠቃቀማቸው ጥንቃቄ ይጠይቃል፡፡

የሰዎችን ስሜት ሊጎዱ የሚችሉ፣ የማስጨነቅና የማሳዘን ተጽዕኖ ያላቸው፣ በማህበረሰቡ ዘንድ እንደ ነውር የሚቆጠሩና ለመልካም ስነምግባር ተጻራሪ የሆኑ የመረጃ ይዘቶች «ለተሟላ ዘገባ» ሲባል «እንደወረዱ» ሊቀርቡ አይችሉም፡፡ በግጭት ውስጥ ጾታዊ ጥቃት የተፈጸመባቸውን ሰዎች ፊት በግልጽ የሚያሳይ ምስል፣ ስምና አድራሻ በዘገባ ውስጥ ላይካተት ይችላል፡፡ በግጭት ውስጥ ተዋናይ የሆኑ ሟችና ገዳይን በሀይማኖታቸው ወይም በብሔረሰባቸው ለይቶ መጥቀስ ተገቢነትን በጥንቃቄ ማየት ያስፈልጋል፡፡[13]

ግጭት ሊፈጥሩ፣ ሁከትና ነውጥ ሊያስነሱ ወይም ሊያባብሱ ይችላሉ፡፡ ዘገባዎች ምሉዕ እንዲሆኑ የሚጠበቀው ከማህበረሰብ ሰላም፣ ደህንነትና ጥቅም አንጻር ብቻ መሆኑን በመገንዘብ መገናኛ ብዙሀን ከዘገባዎቻቸው ውስጥ ያሉ ምስሎች፣ መግለጫዎች፣ የሰዎችና የማህበረሰብ ስሞችና መለያዎች ጥላቻን፣ ግጭትን፣ ሁከትንና ነውጥን ሊያስከትሉ ወይም ሊያባብሱ እንደሚችሉ ጥርጣሬ ከተሰማቸው ከዘገባቸው ዝርዝር ውስጥ እንዲወጡ ማድረግ የተሻለ አማራጭ ሊሆን ይችላል፡፡[14]

### ተግባራት

- በግጭት ዘገባዎቻችሁ ውስጥ መልካቸው በምስል ቢታይ እንዲሁም ስምና አድራሻው ቢጠቀስ ለአካላዊና ስነልቦናዊ ጥቃት ሊጋለጡ፣ መገለል፣ አድልኦና በደል ሊደርስባቸው የሚችሉ የዜና ምንጮችን ወይም የዜና ይዘት የሚያካትታቸውን ተጎጂ ግለሰቦችን ማንነት በግልጽ የሚያሳይ መረጃ ከማካተት ተቆጠቡ፡፡
- በግጭቶች አካባቢ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች ስለ አንድ ግጭት በሚሰጡት መረጃ ላይ ተመስርታችሁ ስትዘግቡ የሰዎቹን መልክ፣ ስም፣ አድራሻና ሌሎች መለያዎች መግለጽ በግለሰቦቹ እንዲሁም በማህበረሰባቸው አባላት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል የምንጮችን ማንነት በግልጽና በዝርዝር አትግለጹ፡፡
- በግጭት ዘገባ ውስጥ ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ምንጮችን ስም አትጥቀሱ ወይም በተቀየረ ስም ተጠቀሙ፡፡ በምስላቸው ላይ ፊታቸው በግልጽ ተለይቶ እንዳይታወቅና ድምጻቸውን መለየት እንዳይቻል የሚያደርጉ ዘዴዎችን ተጠቀሙ፡፡
- አንድ የግጭት ዘገባ በሁለት የተለያዩ ሀይማኖት ተከታዮች፣ በሁለት ብሄረሰብ አባላት ወይም በግልጽ በተለዩ ሁለት የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል የተከሰተና የሰዎች ሞት፣ መቁሰልና የንብረት ውድመት  የተከሰተ ከሆነ የሞቱ፣ የቆሰሉና ንብረታቸው የወደመ ሰዎችን በማህበረሰባዊ ማንነታቸው ዝርዝሮ ማቅረብ ለግጭቱ መባባስ አስተዋጽኦ ሊኖረው ስለሚችል የማንነት ዝርዝር መግለጫ ከማካተታችሁ በፊት ደጋግማችሁ አስቡ፡፡

---

[13] የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን/የተመድ የሴቶች ተቋም-ኢትዮጵያ (UNWomen) - ሥርዓተ-ጾታን ያገናዘበ የመገናኛ ብዙሀን አሰራር ሰነድ፡፡ (የህትመት ዓመትና ቦታ ያልተካተተበት)፡፡

[14] Howard, Ross. (2008). Conflict Sensitive Journalism: A Handbook. (Special Edition Kenya). International Media Support.

## መርህ 9
## ስሜታዊና የተጋነነ ቃላትን ከመጠቀም ተቆጠቡ

### አጭር መግለጫ
የጋዜጠኞች የሁሌም ፍላጎት ተደራሲዎቻቸውን የሚስቡ ዘገባዎችን ማቅረብ ነው፡፡ ዘገባዎችን ሳቢ ከሚያደርጓቸው አላባውያን መካከል ቋንቋ ይገኛል፡፡ በዚህ ምክንያት የተመረጡ ትኩረት ሳቢ ቃላት ያሉባቸው የዜና ርዕሶችን ማየት የተለመደ ነው፡፡ ዝርዝር የዘገባ ይዘቶችንም በስሜት ቀስቃሽ ቋንቋ የማቅረብ ዝንባሌ አለ፡፡

ሆኖም የቋንቋ አጠቃቀም ጥንቃቄ ከጎደለው የዘገባ ሚዛናዊነትንና ትክክለኛነትን በመጉዳት ተዓማኒነትን ሊያሳጣ ይችላል፡፡ በተለይም በግጭት ዘገባ ውስጥ ስሜታዊና የተጋነኑ ቃላት ይበልጥ ጎጂ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በግጭት ውስጥ የደረሱ አደጋዎች፣ የሰዎች ሞትና ጉዳት የሚዘገቡበት ቋንቋ ለተደራሲው የተዛባ ስዕል ከመስጠት ባሻገር ግጭትን የማስፋፋት፣ የቁጭት፣ የቂምና በቀል ስሜት የመፍጠር ተጽዕኖው የሚናቅ አይደለም፡፡

አንዳንድ መገናኛ ብዙሀን ከግጭቶች ወይም ከህገወጥ ታጣቂ ቡድኖች እርምጃዎች ጋር የተያያዙ ግድያዎችን ለመግለጽ ከተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች አባላትና መሪዎች የሚመነጩ አባባሎችን ወይም የራሳቸውን የተጋነኑና ግልጽ ያልሆኑ ቃላት ይጠቀማሉ፡፡ ከእነዚህ ቃላት መካከል፣ ለምሳሌ ያህል ጭፍጨፋ፣ ርሸና፣ እልቂት፣ እና ዘር ማጥፋት የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በእነዚህ ቃላት የሚጠቀሙ ጋዜጠኞች (በተለይም ከማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን) ፍላጎታቸው የብዙ ሰዎች መገደልን ለመግለጽ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ቃላቱ በትክክል «የሰዎችን መገደል» ከመግለጽ በላይ ያዘሏቸው የታጨቁና የተጋነኑ ትርጉሞች ስላሉ ቀላልና ቀጥተኛ ቃላትን መጠቀም ይመረጣል፡፡

ይህ ማለት ጋዜጠኞች በግጭቶች ውስጥ ወይም በህገወጥ ታጣቂዎች በሰዎች ላይ የሚደርሰውን ሞትና ጉዳት አቃልለው ያቅርቡ ማለት አይደለም፡፡ የሰዎች ሞትና ስቃይ ያለበት ዘገባ በራሱ አስደንጋጭና አሳዛኝ በመሆኑ እንዲህ ያለውን ክስተት በሚመለከት እውነተኛና ትክክለኛ መረጃ ከስሜትና ከግነት ነጻ በሆነ ግልጽ ቋንቋ ያቅርቡ ማለት ነው፡፡ [15]

### ተግባራት
- ስለ ግጭት ስትዘግቡ ከስሜትና ከግነት ነጻ የሆኑ ቃላትን ተጠቀሙ፡፡
- ብዙ ትርጉሞች በውስጣቸው በተሸከሙና ግልጽነት በጎደላቸው ቃላት ከመጠቀም ተቆጠቡ፡፡
- ስሜትና ግነት ያዘሉ ቃላትን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ካመናችሁ ቃላቱ መረጃ የማዛባትና በተደራስያን ዘንድ የተሳሳተ ግንዛቤ የማስከተል ተጽእኖ እንዳይኖራቸው ጥንቃቄ አድርጉ፡፡
- የዜናችሁ አርዕስት በዘገባዎቻችሁ ዝርዝር ውስጥ ያሉትን ይዘቶች በትክክል የሚወክሉ መሆናቸውን እርግጠኛ ሁኑ፡፡
- ከዝርዝር የዜና ይዘቶች ጋር የማይጣጣሙ የዜና አርዕስት ለጊዜው አንባቢን ወይም አድማጭን ሊስቡ ቢችሉም የዜናውን ይዘት የማይወክሉ መሆናቸው ሲታወቅ ተዓማኒነትን የመጉዳት ውጤት ስለሚያስከትሉ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡
- የሰዎችን መገደል ስትዘግቡ አሀዛዊ (ቁጥራዊ) መረጃ ተጠቀሙ፡፡ ትክክለኛ ቁጥሮችን ማግኘት የማይቻል ከሆነ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ግምት (ለምሳሌ- ከ4 እስከ 7 የሚደርሱ) የሚል የታዛቢ ምንጮች መረጃ ለመጠቀም ሞክሩ፡፡

---
[15] Howard, Ross. (2008). Conflict Sensitive Journalism: A Handbook. (Special Edition Kenya). International Media Support.

## መርህ 10
## የጥላቻ ንግግሮችን አስወግዱ

### አጭር መግለጫ

"የጥላቻ ንግግር" ማለት በአንድ ሰው ወይም በተወሰነ ቡድን ማንነት ላይ ያነጣጠረ፣ ብሔርን፣ብሔረሰብንና ህዝብን፣ ሃይማኖትን፤ ዘርን፣ ጾታን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ ሆን ተብሎ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን የሚያነሳሳ ንግግር ነው፡፡[16]

የጥላቻ ንግግሮች ልዩነቶችን ወደ ግጭት፣ ግጭትን ወደ ነውጥ ሊወስዱ የሚችሉ የተግባቦት ችግሮች ናቸው፡፡ አሉታዊ ስሜት በመቀስቀስ የጋራ መግባባት እድሎችን የማጥበብ አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡[17]

መከባበርን፣ መቻቻልንና በሰላም አብሮ መኖርን ይገዳደራሉ፡፡ ልዩ ልዩ ተጋላጭነት ያላቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች ማጥቂያ መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ኢእኩልነት ዘላቂ ሆኖ እንዲቀጥል፣ ውጥረት እንዲበረታ ያደርጋሉ፡፡ በዲሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች ላይ ስጋት ይደቅናሉ፡፡ ስለዚህ በሰላም ግንባታና ግጭቶችን በመፍታት ሂደት አዎንታዊ ሚና ያላቸው መገናኛ ብዙሀን የጥላቻ ንግግሮችን በዘገባዎቻቸው ውስጥ አያካትቱም፡፡ ከዘገባ ውስጥ የጥላቻ ንግግሮችን ማስወገድ ከመገናኛ ብዙሀን ሙያዊ ነጻነት የሚመነጭ ኃላፊነት ነው፡፡[18]

### ተግባራት

- ማንኛውንም በዘገባ ውስጥ የሚጠቀስ ግለሰብን፣ ቡድንን ወይም የማህበረሰብ አካልን በጥላቻ የሚገልጽና ለመገለል፣ ለመድልኦና ለጥቃት የሚያጋልጥ ማንኛውንም አሉታዊ ቅጽልና መግለጫ አትጠቀሙ፡፡
- ግጭትን በሚመለከቱ የቀጥታ ቃለመጠይቆች ፖለቲከኞች፣ በግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች ተወካዮችና አስተያየት ሰጪዎች ሀሳባቸውን መግለጽ ከመጀመራቸው በፊት ማንኛውንም ወገን በጥላቻ ንግግር ከመጥቀስ እንዲቆጠቡ በማሳሰብ ጀምሩ፡፡
- ፖለቲከኞች፣ የህዝብ አስተያየት መሪዎች፣ ዜጎችና የተለያዩ ባለድርሻዎች የሚጠቀሙባቸውን የጥላቻ ንግግሮች ዘገባዎቻችሁ ውስጥ እንዳይገቡ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡
- በግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች እርስ በርስ በጠላትነት በመፈራረጅ የሚለዋወጧቸው የጥላቻ ንግግሮች፣ ዛቻዎችና ቁጣ ቀስቃሽ ንግግሮች ግጭትን ሊያባብሱ ስለሚችሉ እንዳሉ ቃል በቃል ከማስተላለፍ ተቆጠቡ፡፡

---

16 ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (2012) አዋጅ ቁጥር 1185/2012 ዓ.ም የጥላቻ ንግግርን እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ. አዲስ አበባ፡፡

17 European Institute of Peace. Fake news misinformation and hate speech in Ethiopia: A vulnerability assessment. (12 April 2021).

18 United Nations. 2019. United Nations Strategy and Plan of Action on Hate Speech. UN: May 2019.

# መርህ 11
# የሀሰተኛ ዜናና መረጃ ስርጭትን ግቱ

## አጭር መግለጫ

*"ሐሰተኛ መረጃ" መረጃው ሐሰት የሆነና የመረጃውን ሐሰተኝነት በሚያውቅ፣ ወይም መረጃውን የሚያሰራጨው ሰው ካለበት አጠቃላይ ሁኔታ አንጻር የመረጃውን እውነተኝነት ለማጣራት በቂ ጥረት ሳያደርግ የሚሰራጭ ሁከት ወይም ግጭት የማስነሳት፣ ወይም ጥቃት እንዲደርስ የማድረግ ዕድሉ ከፍ ያለ ንግግር ነው፡፡*[19]

*የመረጃ ቴክኖሎጂ መስፋፋት ሀሳብን በነጻ የመግለጽ አቅምን የማሳደጉን ያህል ሀሰተኛ ዜናና መረጃ በሰፊው እንዲሰራጭ አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ በዚህ ምክንያት እውነተኛ፣ ትክክለኛና ሚዛናዊ ዘገባ የማሰራጨት ሙያዊ ተግባር ከፍተኛ ተግዳሮት ገጥሞታል፡፡ የሚሰራጩ የዜናና የመረጃ ጥንቅሮች በግለሰቦችና በህብረተሰብ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የመከላከል የኃላፊነት እሴት ፈተና ላይ ወድቋል፡፡ ሀሰተኛ ዜናና መረጃ በሰላም ግንባታና ለግጭቶች አዎንታዊ መፍትሄ በማስገኘት ሂደት ላይ ከባድ ተግዳሮት ሆኗል፡፡*

*መገናኛ ብዙሀን ከማንኛውም ጊዜ በላይ ከየትኛውም ምንጭ የሚያገኙትን ዘገባም ሆነ መረጃ እውነተኝነት፣ ትክክለኝነትና ሚዛናዊነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሙያዊ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ ዜናና መረጃ በልዩ ልዩ የቴክኖሎጂ አማራጮች በማሰራጨት ታዋቂነትና ተዓማኒነት ካተረፉ መገናኛ ብዙሀን፣ ተቋማትና ግለሰቦች ሁሉ የሚገኙ ይዘቶችን እንዳሉ በመቀበል ከማሰራጨት በፊት እውነተኝነታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ጋዜጠኞች እንደ መረጃ ምንጭ የሚጠቀሙባቸውን ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን እውነተኛነት ማረገገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡*

*የመረጃ እውነተኛነትና ትክክለኛነት እንደምንጮቹ የተዓማኒነት ደረጃ ይወሰናል፡፡ በይፋ እንደግለሰብ የሚታወቁና በህግ ሊጠየቁ የሚችሉ ሰዎችን፣ ተቋማትንና መንግስታዊ ድርጅቶችን እንደመረጃ ምንጭ መጠቀም ይቻላል፡፡ ሆኖም ተቋማቱ ሀሰተኛና የተዛባ መረጃ ከማሰራጨት ፍጹም የተቆጠቡ ናቸው ወይም አይዋሹም ማለት ሳይሆን ተቋማዊ ተጠያቂነታቸው የተሻለ ተቀባይነት ስለሚያስገኝላቸው ነው፡፡*[20]

*እውነትን መዘገብ የጋዜጠኝነት የመጀመሪያው ኃላፊነት ነው፡፡ ነገር ግን የመረጃ እውነተኛነት ብቻውን ዜና ለመዘገብ የሚያስችል መመዘኛ አይደለም፡፡ በተለይም ጎጂ ተጽዕኖ ሊኖራቸው የሚችሉ የመረጃ ይዘቶች እውነተኛ ቢሆኑም ከፍ ያለ ጥንቃቄ ይሻሉ፡፡ እውነትን መዘገብ ጎጂ የሚሆንባቸውን አውዶች (ሁኔታዎች) በግልጽ መበየን አስቸጋሪ ቢሆንም የግጭት ዘገባዎች የእውነተኛ መረጃ ስርጭት በግለሰቦች፣ በተቋሞችና በሀገር ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ጉዳቱ በማህበረሰብ አባላት መካከል አለመተማመን፣ ጥርጣሬና ጥላቻ፣ ቂምና በቀል ከማስከተል ጋር የሚያያዝ ሊሆን ይችላል፡፡ ቅራኔዎችንና ግጭቶችን በማወሳሰብ ሁከትና ነውጥን ሊያባብስ ይችላል፡፡*

*ሰላምን ሊያውኩ የሚችሉ የመረጃ ይዘቶች ይሁን ተብለው ወይም በስህተት ተዘጋጅተው የሚሰራጩ ሀሰተኛ የመረጃ ጥንቅሮች ብቻ አይደሉም፡፡ እውነተኛ መረጃም ሰላምን ለማወክ ዓላማ ሊውል ይችላል፡፡ ጉዳት ለማድረስ ይሁን ተብሎ እውነተኛ መረጃ የማሰራጨት ተግባር እንደ አሉታዊ የተግባቦት ተግባር የሚታወቅ ፈርጅ ነው፡፡ ስለዚህ መገናኛ ብዙሀን የሚያሰራጯቸው በእውነተኛ መረጃ ላይ የተመሰረቱ ዘገባዎች ሲሰራጩ በተደራሲዎች ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉት ውጤት ጎጂ አለመሆኑን ወይም አዎንታዊ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡*

---

19 ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (2012) አዋጅ ቁጥር 1185/2012 ዓ.ም የጥላቻ ንግግርን እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ. አዲስ አበባ፡፡

20 Huckerby, Martin. (2005). The Net for Journalists፡ A practical guide to the internet for journalists in developing countries. UNESCO: The Thomson Foundation.

የግጭት፣ የሁከትና የነውጥ ክስተቶችን የሚያሳዩ የግድያና ውድመት ፎቶግራፎችና ተንቀሳቃሽ ምስሎች እውነተኛ ቢሆኑም እንኳ ከአውዳቸው ውጪ የጊዜና የቦታ ለውጥ ተደርጎባቸው አዲስ የተከሰቱ መስለው ሊቀርቡ ስለሚችሉ መገናኛ ብዙሀን በመሰል የመረጃ ጥንቅሮች ከመጠቀማቸው በፊት ከመረጃው እውነተኛነት በተጨማሪ የአውዳቸውን (የቦታ፣ የጊዜና የሁኔታዎች ጥምረት) ትክክለኛነት ማጣራት አለባቸው፡፡

## ተግባራት

- በማንኛውም ሁኔታ የአንድን የዜና ምንጭ የመረጃ ይዘቶች እውነተኝነትና ትክክለኝነት ሳታጣሩ አትዘግቡ፡፡
- የአንድን ዜና ምንጭ መረጃ ትክክለኛነት ሌሎች ተዛማጅ የዜና ምንጮችን በመጠየቅ አረጋግጡ፡፡
- በተለይ ከድረገጽና ማህበራዊ መገናኛ ብዙሀን በሚገኙ የመረጃ ጥንቅሮች ከመጠቀማችሁ በፊት ስለ እውነተኝነታቸውና ትክክለኝነታቸው ደጋግማችሁ አረጋግጡ፡፡
- በድረገጽ መረጃ ውስጥ የተጠቀሱ የመረጃ ምንጮችን ቢያንስ በስልክ በማግኘት የመረጃውን እውነተኝነትና ትክክለኝነት ፈትሹ፡፡
- በአንድ ድረገጽ ወይም ማህበራዊ ብዙሀን መገናኛ ብቻ የሚገኝና በሌሎች ድረገጾች የሌለ የዜና መረጃን ከመጠቀማችሁ በፊት አጠራጣሪ ምልክቶች አለመኖራቸውን መርምሩ፡፡
- እውነተኛነታቸው አወዛጋቢ የሆነ የጽሁፍና የምስል መረጃ ይዘቶች ሲያጋጥማችሁ በግል ድምዳሜ ከመቀጠል ይልቅ በቡድን ምክክር ወስኑ፡፡
- እውነተኛነታቸው ከማያጠራጥር የመረጃ ጥንቅሮች ጋር የተቀላቀሉ ሀሰተኛ የመረጃ ይዘቶች አለመኖራቸውን አረጋግጡ፡፡
- የመረጃ እውነተኛነትን ለማረጋገጥ የዜና ትክክለኝነትን ለማጣራት ከሚሰሩ ተቋማትና ባለሙያዎች ምክር ጠይቁ፡፡
- ባሰራጫችሁት ዘገባ ውስጥ ስህተት ያለባቸው ወይም ሀሰተኛ የሆኑ ይዘቶች ቢገኙ በፍጥነት ማረሚያ በማውጣት ተደራሲዎቻችሁን ይቅርታ ጠይቁ፡፡
- የተሳሳተ ወይም ባለማወቅ ሀሰተኛ ዘገባ አሰራጭቶ ማረሚያ የማያወጣና ይቅርታ የማይጠይቅ የብዙሀን መገናኛ ተቋም በተደራስያኑ ዘንድ ተዓማኒነት ያጣል፡፡ ተዓማኒነታችሁን ለመጠበቅ ሁሌም እውነተኛ፣ ትክክለኛና ያልተዛባ ዘገባ ዘግቡ፡፡ ለስህተቶቻችሁ በፍጥነት እርማት በማውጣት ተደራሲዎቻችሁን ይቅርታ ጠይቁ፡፡

# መርህ 12
# የድህረ-ግጭት ጉዳቶችን ለማከም ትኩረት ስጡ

## አጭር መግለጫ

ወደ ሁከት፣ ነውጥና ጦርነት ያደገ ግጭት በሰላማዊ መንገድ ሊፈታ ይችላል፡፡ ሰላማዊ መፍትሄ የጠመንጃ ተኩስ እንዲያበቃ፣ የሰዎች ስቃይና ዋይታ በጸጥታ እንዲተካና የንብረት ውድመት እንዲገታ ያደርጋል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ነገር ከነውጡና ጦርነቱ በፊት ወደ ነበረበት እንዲመለስ ማድረግ ከባድ ነው፡፡ ነውጥና ጦርነት በሰዎች ስነልቦና ላይ የሚቀር አሻራ ይተዋሉ፡፡

ብዙዎች በራሳቸው ላይ በቀጥታ በደረሱ ወይም በወገኖቻቸው ላይ ደርሰው በተመለከቷቸው አሰቃቂ ጥቃቶች ምክንያት የስቃይ ሰለባ ሆነው ለረጅም ጊዜ በስነልቦና ቀውስ ውስጥ ይቆያሉ፡፡ ውስጣዊ መረበሽ፣ ፍርሀት፣ የበደል፣ የግፍና የመከራ ትውስታዎች ከውስጣቸው በቶሎ አይጠፉም፡፡ ወደ ጤናማና መደበኛ ህይወት ለመመለስ ይቸገራሉ፡፡

የ«ድህረ-ግጭት» ጽንሰ ሀሳብ ሁሉንም ሊያግባባ የሚችል አንድ ብያኔ ባይኖረውም፣ በሁከት፣ ነውጥና ጦርነት ውስጥ ያለፉ ማህበረሰቦች ግጭት ካስከተለባቸው ሰብዓዊ ቀውስ፣ ጥፋትና ውድመት ለማገገምና ለመረጋጋት፣ የመልሶ ማቋቋምና የመልሶ ግንባታ የሚያከናውኑበትን ጊዜ የሚገልጽ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ የግጭት ፍጻሜን ተከትሎ የሚመጣ ወስብስብ ሂደትንና የሚከናወኑ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ያካትተታል፡፡ ተቋማትን መልሶ ከማደራጀት፣ ከማዋቀርና ጥርጣሬን በማስወገድ መተማመንን፣ መግባባትንና ዘላቂ ሰላምን ከመገንባት ሂደት ጋር ይያያዛል፡፡

የድህረ-ግጭት ተግባራት በግጭት ወቅት የተፈጠሩ ስነልቦናዊ ጉዳቶች የሚታከሙባቸውና ተከታታይነት ባለው ማህበረሰባዊ ውይይት ወደ መግባባትና እርቅ ጉዞ የሚደረግባቸውን ክንውኖች ሂደት ያካትታሉ፡፡ ሂደቱ የማህበረሰቡን አባላት የሚከፋፍሉና የሚያጋጩ ጉዳዮች ተድበስብሰው እንዳይቀሩ በማድረግ ግጭት እንዳያገረሽ ማድረግን ይጨምራል፡፡ በድህረ-ግጭት አውድ ውስጥ የሚገኝ ማህበረሰብ የግጭት መንስዔ የሆኑ መሰረታዊ ችግሮችን ለመፍታት ቁርጠኛ መሆን ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ ከወሳኝ ተግባራት እንደዋነኛው ይቆጠራል፡፡[21]

የድህረ-ግጭት ማህበረሰብ ከግጭት ያተረፈው የቂም ቁስል እንዲሽር፣ ካሳለፈው የሁከት፣ የነውጥና የጦርነት ጥፋትና ውድመት እንዲማር፣ መጪውን ዘመን መልካም የጋራ ግብ መምቻ አድርጎ በማሰብ ወቅታዊ ህይወቱን እንዲመራ ለማድረግ የሚያግዙ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡ ይህም ስላለፈው ግጭት መርሳትን አይደግፍም፡፡ ይልቁንም ሁሉቱንም የግጭት ወገኖች የሚወክሉ ግፍ የተፈጸመባቸውንና ግፍ የፈጸሙትን ተዋንያን ድርጊት በመተንተን ተመሳሳይ ጥፋት እንዳይደገም በማስተማር ላይ የሚያተኩሩ መድረኮችን ያበረታታል፡፡ ሂደቱም በማህበረሰቡ ውስጥ የተፈጠረው ስነልቦናዊ ጉዳት በትክክል ለማከምና ማህበረሰባዊ እርቁንም እውነተኛ ለማድረግ የማይተካ እርምጃ ነው፡፡

## ተግባራት

- ከጦርነት ፕሮፓጋንዳ ውጡ፡፡
- በግጭት ወቅት ትጠቀሙባቸው የነበሩትን ጠላትነትን የሚገልጹ ቃላት መጠቀማችሁን ተዉ፡፡
- በድህረ-ግጭት ዘገባዎቻችሁ ውስጥ ተፋላሚ የነበሩ ወገኖችን አሸናፊና ተሸናፊ አድርጋችሁ በመሳል ከፋፋይና ቁጭት ቀስቃሽ መልዕክት ከማስተላለፍ ተቆጠቡ፡፡

---

21 Orgeret, Kristin Skare and William Tayeebwa (eds.) 2016. Journalism in conflict and post-conflict conditions: Worldwide perspectives. Nordicom: University of Gothenburg.

- የድህረ-ግጭት የዜና ምንጮች የሆኑ ባለስልጣኖች፣ የፖለቲካ፣ የህዝብ አስተያየትና የማህበረሰብ መሪዎች ቋንቋ ወደ መግባባትና እርቅ በሚወስድ አዎንታዊ ቅኝት ውስጥ መሆኑን አረጋግጡ፡፡ የጥላቻ ንግግሮችን ተቀብላችሁ ከማስተላለፍ ተቆጠቡ፡፡
- በዘገባዎቻችሁ ሁሉ አካታች ሁኑ፤ የሁሉም ወገኖች ተሞክሮ፣ ሀሳብና አስተያየት ከተደራስያን እንዲደርስ እድል ስጡ፡፡
- በግጭት ውስጥ የነበሩ ወገኖችን ወደ መግባባትና እርቅ በሚወስዷቸው አርዕስተ ጉዳዮች ላይ አተኩሩ፡፡
- ከግጭት መቆም በኋላ የተከተለው ሰላም በማህበረሰቡ አባላት ስሜት፣ ስነልቦናና አስተያየት ላይ የፈጠረውን አዎንታዊ ሁኔታ በተከታታይ ዘግቡ፡፡
- በግጭት ወቅት አካላዊና ስነልቦናዊ ጥቃቶች የደረሱባቸው ሴቶችና ህጻናት ሁሉን አቀፍ ተከታታይ ህክምናና መልሶ የማቋቋም ድጋፍ ማግኘታቸውን አረጋግጡ፡፡
- ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶችና ህጻናትን የሚመለከቱ ተከታታይ ዘገባዎችን ከስነልቦናና ህክምና ባለሙያዎች እንዲሁም ተቋማት ጋር በመተባበር አዘጋጁ፡፡
- በድህረ-ግጭት የመልሶ ማቋቋምና መልሶ ግንባታ ሂደት ውስጥ ሴቶች ተገቢ ሚና እንዲኖራቸው ለሚያደርጉና ለሚያበረታቱ ይዘቶች ትኩረት ስጡ፡፡
- የድህረ-ግጭት የመልሶ ማቋቋምና የመልሶ ግንባታ ስራዎችን የሚመለከቱ ሰፊ የዜና፣ የትንታኔና የትረካ ዘገባ ሽፋን ስጡ፡፡
- በግጭት ውስጥ በነበሩ ወገኖች መካከል ያለመተማገንና የግጭት መንስዔዎች የሆኑ መሰረታዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚደረጉ ጥረቶችን በትኩረት ዘግቡ፡፡
- ዘላቂ ሰላምን ሊያመጣ የሚችለው ለመሰረታዊ ችግሮች መፍትሄ ማግኘት መሆኑን ለሚያሳውቁ ውይይቶችና ትንታኔዎች በቂ ሥፍራ ስጡ፡፡
- በግጭት ውስጥ በነበሩ ወገኖች መካከል የተፈጠረው የቂም ቁስል እንዲሽር፣ ካለፈው ክፉ ተሞክሮ ሁሉም ትምህርት እንዲወስድና ስለመጪው የጋራ ግብ በማሰብ የዛሬ ህይወቱን እንዲመራ የሚያግዙ ተከታታይነት ያላቸው ጥልቅ ዘገባዎች እያዘጋጃችሁ አሰራጩ፡፡
- በግጭት ውስጥ ግፍ የፈጸሙና ግፍ የተፈጸመባቸውን ሰዎች የሚመለከቱ ዘገባዎችን ስትሰሩ የሁሉንም ወገኖች ድምጽ ማካተታችሁን አረጋግጡ፡፡
- ስላለፉ የግፍ ድርጊቶች ስትዘግቡ ዓላማችሁ ካለፈው ግጭት ሰዎች ትምህርት እንዲያገኙና ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈጸም ለማድረግ ብቻ መሆኑን እርግጠኛ ሁኑ፡፡

## መርህ 13
## ውይይትና ምክክር አሰተናግዱ

### አጭር መግለጫ

በማህበረሰብ ውስጥ ሁሌም የሀሳብ ልዩነት አለ፡፡ ልዩነቱ የተለያዩ የፖለቲካ፣ የፖሊሲና የአደረጃጀት አቅጣጫዎችን የሚከተሉ በበርካታ ዘርፎች የተደራጁ ተፎካካሪ ቡድኖችን ይፈጥራል፡፡ ልዩነቶቹ የሚፈጥሯቸው ቡድኖች መኖራቸው በራሱ ችግር አይደለም፡፡ የሁሉም ወገኖች ፉክክር ሰላማዊ መንገዶችን የሚከተል ከሆነ ለሀገር እድገት አዎንታዊ አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል፡፡ ፈተና የሚሆነው ፉክክሩ ሁከትና ነውጥን ከቀላቀለ ነው፡፡

አንዳንድ ሁኔታዎች የጋራ ውይይትና ምክክር የሚሹ አወዛጋቢ ጉዳዮችን ያስከትላሉ፡፡ ግጭት ይከሰታል፡፡ መሳሪያ የታጠቁ ቡድኖች ወደ ውጊያ አማራጭ ሊያመሩ ይችላሉ፡፡ እንዲህ ባሉ ሁኔታዎች መወያየትና መመካከር ብዙ ጥፋትና ውድመት እንዳይደርስ ለመከላከል ያስችላል፡፡ ግጭቶች አሳሳቢ በሆኑባቸውና ጉዳት ባደረሱባቸው የተለያዩ የዓለም ክፍሎች አገራዊ ውይይትና ምክክር የሰላማዊ መፍትሄ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ አገራዊ ምክክር ማለት ማህበረሰባዊ ልዩነቶች የሚፈጥሯቸውን እንደ ግጭት፣ ጦርነትና ማህበራዊ ቀውስ ያሉ አገር አቀፍ ስጋቶችን በሚመለከት ሰፊ ባለድርሻዎች በውይይት ከጋራ መግባባት ለመድረስ የሚገለገሉበት ይፋዊ ፖለቲካዊ ሂደት ነው፡፡ የኢትዮጵያ አገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ (ቁጥር 1265/2014) እንደሚለው የኮሚሽኑ ዓላማ በሀገሪቱ «የሚካሄዱት ሀገራዊ ምክክሮች በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍልች መካከል እንዲሁም በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል፣ መተማመን የሰፈነበትና አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር በሚያስችል አግባብ ውይይቶቹ እንዲካሄዱ ሥርዓት መዘርጋት» ነው፡፡

ውይይትና ምክክር ከፍተኛ ጥንቃቄ፣ ትዕግስት፣ ትብብር፣ መቻቻል፣ መከባበር፣ ቁርጠኝነት ፣ ሙያዊ ብቃትና አካታች አቀራረብ የሚሻ በተለያዩ ዘርፎችና እርከኖች የሚከናወንና ጊዜ ሊወስድ የሚችል ውስብስብ ሂደት ነው፡፡ አወዛጋቢ በሆኑ የህገመንግስት፣ የህግ፣ የፖሊሲ፣ የአስተዳደር፣ የፖለቲካዊ አወቃቀርና፣ ሌሎች ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ከመግባባት ለመድረስ ተመራጭ ዘዴ ነው፡፡ ሂደቱ ስኬታማ እንዲሆን ሁሉን አካታች፣ ግልጽና ከሸፍጥ የፀዳ፣ በሀቅና በገለልተኝነት፣ በአገራዊ አውድ ውስጥ የተመቻቸ አካሄድን ይሻል፡፡[22]

አካታችነት[23] የሂደቱ መሰረታዊ መመዘኛ የመሆኑን ያህል በአገራዊ ውይይትና ምክክር ውስጥ በስኬት የሚተገበረው ፈታኝ ተግዳሮቶችን በማለፍ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም እያንዳንዱ ባለድርሻ ሊያነሳ ከሚችለው ቅድመሁኔታና ምላሹም ሌሎች ባለድርሻዎችን ከሂደቱ የማያስወጣ ከመሆኑ ጋር ይያያዛል፡፡ ሂደቱ በሚፈታቸው ችግሮችና በመፍትሄው ስነዘዴ ላይ የጋራ መግባባት መፍጠርንም ይጠይቃል፡፡

በየመኖሪያ አካባቢው ያለውን ሰፊ ማህበረሰብ ማሳተፍ ሌላው የስኬት መመዘኛ ነው፡፡ ሂደቱ የየዘርፉን ልሂቃን ብቻ በፖለቲካው ላዕላይ ምህዳር ላይ ሰብስቦ በማወያየትና በማመካከር ከቀረ ጽኑ መሰረት ሊሆነው የሚችለውን ህዝባዊ ተሳትፎ ያጣል፡፡ ተዓማኒነትም አይኖረውም፡፡ ስለዚህ ህዝብ በውይይትና ምክክሩ ውስጥ ሰፊ ድርሻ ሊኖረውና ተሰሚነት ሊያገኝ ይገባል፡፡ ሲቪል ማህበራት፣ ምሁራን፣ የሙያ ማህበራት፣ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች፣ መገናኛ ብዙሀን፣ የማህበረሰብ መሪዎች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞችና ሌሎችም በሂደቱ ውስጥ ድርሻ መያዛቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ተሳትፎን የሚያበረታቱ መልዕክቶችን በማሰራጨት መቀስቀስ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ የአገራዊ ምክክር ስኬት ልክ የሂደቱን መኖር በሚያውቀው፣ በሚሳተፈውና በሚደግፈው ህዝብ ልክ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡[24]

---

[22] United Nations Development Program (n.d) Community Dialogue for Sustainable Peace: A Handbook for Generating Citizens' Engagement for Sustained Dialogue on Conflict Prevention, Social Cohesion and Integration. UNDP. , [23] የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፡፡ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1265/2014፡፡ ነጋሪት ጋዜጣ ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፳ አዲስ አበባ ጥር 5 ቀን 2014 ዓ.ም፡፡

[24] Berghof Foundation. (2017). National Dialogue Handbook: A Guide for Practitioners. Berlin: Berghof Foundation Operations GmbH

አገራዊ ምክክር በአዳራሾችና በዝግ በሚካሄዱ ስብሰባዎች ብቻ አይጠናቀቅም፡፡ መገናኛ ብዙሀን ለሂደቱ ስኬት የሚያበረክቱት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ይልቁንም በጥንቃቄ በተጠና የመገናኛ ብዙሀን አጠቃቀም ስልት ሂደቱን ማገዝ ይቻላል፡፡ መገናኛ ብዙሀን በባለድርሻዎች መካከል እንዲሁም በባለድርሻዎችና በህዝብ መካከል የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥና ውይይት እንዲኖር በማድረግ ምክክሩ እንዲቀላጠፍ አዎንታዊ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ለብዙ ህዝብ ተደራሽ የሆኑ መገናኛ ብዙሀንን በመለየት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

## ተግባራት

- የአገራዊ ምክክር ስኬት ካለመገናኛ ብዙሀን ተሳትፎ ሊታሰብ የማይችል በመሆኑ ሂደቱን የሚመለከቱ ሰፊ የዘገባ ሽፋን ስጡ፡፡
- አገራዊ ምክክርን አስፈላጊ የሚያደርጉ ግጭቶችንና ማህበራዊ ቀውሶችን ምንነት ከመነሻቸው ሊያስረዱ የሚችሉ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበረሰባዊ ዳራዎችን (የቀደሙ ሁኔታዎችን) የሚገልጹ የመረጃ ይዘቶችን በዘገባዎቻችሁ ውስጥ ተጠቀሙ፡፡
- ስለ አገራዊ ምክክር በዓለም አቀፍ ደረጃ የተዘጋጁና ኢትዮጵያን መሰረት አድርገው የተሰናዱ ተዛማጅ ሰነዶችን የሚመለከቱ ትምህርታዊ ውይይቶችን አዘጋጁ፡፡ ስለ አገራዊ ምክክር ምንነት፣ ስለሂደቱ፣ ስለተግዳሮቶቹና ስኬታማ ለመሆን ስለሚያስፈልጉ የባለድርሻዎች ሀላፊነቶች አወያዩ፡፡
- በአገራዊ ምክክር አውድ ውስጥ አበይት አጀንዳዎችን ለህዝብ አሳውቁ፡፡ ሂደቱ የሚገኝበትን ደረጃ እየተከታተላችሁ ዘግቡ፡፡
- ስለሂደቱ ህዝብ ያለውን ግንዛቤ የሚፈትሹ ዘገባዎች ስሩ፡፡ ስለአገራዊ ምክክሩ የህዝብ ግንዛቤን ለማሳደግ የሚችሉ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን ፈትሹ፡፡
- አገራዊ ምክክሩ ለእያንዳንዱ ዜጋ ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም በዘገባዎቻችሁ ውስጥ በተለያዩ የመረጃ ምንጮች እንዲገለጽ አበረታቱ፡፡
- የዘገባ ዝግጅቶቻችሁን በደረቅ ዜና ብቻ አትወስኑ፡፡ ጥልቅ ቃለመጠየቆችን፣ ተራኪ ዘገባዎችን፣ ሀተታዎችን፣ ርዕሰአንቀጾችን፣ የቀጥታ ስልክ ምልልሶችን፣ አስተያየቶችንና ሌሎችንም የዘገባ ዘውጎች እየቀያየራችሁ ተጠቀሙ፡፡
- የአገራዊ ምክክር ሂደቱን አካታችነት የሚፈትሹ ዘገባዎች ስሩ፡፡ የሂደቱን አካታችነት ስትመረምሩ ዘገባዎቻችሁ አካታች መሆናቸውን አረጋግጡ፡፡
- የአገራዊ ምክክር አካታችነት ሁሉንም ተፎካካሪ ወገኖች፣ የፖለቲካ ማህበራት ተወካዮችና ተጠሪዎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ አባላትን፣ ባለሙያዎችና የማህበረሰብ መሪዎችን ብቻ የሚመለከት አለመሆኑን አስታውሱ፡፡ ሰፊው ህብረተሰብ በየመኖሪያ አካባቢው የአገራዊ ምክክሩ ተሳታፊ ሆኖ ድምጹን ማሰማት መቻሉን አረጋግጡ፡፡
- ሂደቱን ካለው አገራዊ ዓላማና ትርጓሜ አንጻር በህዝብ ተሳትፎ እንዲታገዝ ለሚረዱ ዘገባዎች ሰፊ ስፍራ ስጡ፡፡ የሂደቱ ባለድርሻነታችሁን የሚያረጋግጡ ጥልቅ ዘገባዎች ሰርታችሁ አሰራጩ፡፡
- በአገራዊ ምክክር ውስጥ አካታችነት በመኖሪያ አካባቢዎች በሚካሄዱ ህዝባዊ ውይይቶች የሚረጋገጥ ቢሆንም ህዝብ ወጥነት ያለው አንድ ዓይነት ስብስብ ባለመሆኑ በውስጡ እንደ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞችና በልዩ ልዩ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የማህበረሰብ አካላት ያላቸውን የተሳትፎ ደረጃ መርምሩ፡፡
- በምክክር ሂደት ውስጥ ልዩ ልዩ ባለድርሻዎች በሚያካሂዷቸው ውይይቶች ውስጥ ተጀምረው ያልተቋጩና ይፋ ቢወጡ ሂደቱን ሊጎዱ ወይም ሊያበላሹ የሚችሉ ኃላፊነትና ጥንቃቄ የሚሹ የመረጃ ይዘቶችን ይፋዊ ካልሆኑ ምንጮች ወስዳችሁ ስትዘግቡ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡ ቢቻል በይፋዊ የመረጃ ምንጮች ተጠቀሙ፡፡

## መርህ 14
## ስለ ሰላም አውቃችሁ አሳውቁ

### አጭር መግለጫ

ሰላም የግጭት ፣ የሁከት ፣ የብጥብጥና የጦርነት አለመኖር ብቻ አይደለም ፡፡ የሰላም ትርጉም ከዚህም ይሰፋል፡፡ ሰላም በማህበረሰብ ውስጥ የማንኛውም ዓይነት ሁከት አለመኖር ነው፡፡ ሁከት ፍትህና እኩልነትን የሚጻረሩ ሁሉም ዓይነት ማህበራዊ ግንኙነቶችን ያካትታል፡፡ የሰዎች መሰረታዊ ፍላጎቶች በህይወት መኖር፣ ምጣኔያዊ ደህንነት፣ ነጻነትና መከበር ናቸው፡፡ የእነዚህ ሁሉ መሟላት የሰላም መሰረት ነው፡፡[25]

የእነዚህ ተጻራሪ ሁኔታዎች ሞት፣ መከራ፣ ጭቆናና መገለል ናቸው፡፡ የሰዎች መሰረታዊ ፍላጎቶችን የሚጻረሩት ሁኔታዎች የሚፈጠሩት በሦስት የሁከት ዓይነቶች ነው፡፡ እነርሱም ቀጥተኛ ሁከት (ሰዎችን በጦር መሳሪያ መጉዳትና መግደል)፣ መዋቅራዊ ሁከት (በተበላሸ ማህበራዊ መዋቅር ምክንያት የሰዎች በድህነት፣ በረሀብና በበሽታ መሰቃየትና መሞት፤ መብቶቻቸው ተነፍገው በራሳቸው ኑሮ ላይ እንዳይወስኑና እንዲገለሉ ማድረግ)፣ የባህል ሁከት (ቀጥተኛና መዋቅራዊ ሁከቶች በብሄረተኝነት፣ በዘረኝነት፣ በሥርዓተ-ጾታና በሌሎችም የተዛቡ ማህበራዊ ስርዓቶች ምክንያት የሚፈጠሩ) ናቸው፡፡

በተጨማሪም የጨቋኝ አሉታዊ ማህበረሰባዊ እውነታዎች አለመኖር ብቻውን ሰላምን አያረጋግጥም፡፡ ከዚህም በላይ ሰዎች ካለፈና በወቅቱ ካለ ሁከት እፎይታ የሚያገኙበትና ለወደፊቱም ሁከት እንዳይኖር ዋስትና የሚሆኗቸው ማህበረሰባዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መኖር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከማህበረሰብ የተዛባ መዋቅር ጋር የተያያዙ የሰላም ተጻራሪ ችግሮች የሚፈቱት ከማህበረሰባዊ መዋቅሩ መስተካከል ጋር ነው፡፡[26]

ግጭቶች ተቀስቅሰው ወደ ሁከትና ነውጥ በሚሸጋገሩበት ወቅት ለችግሩ መንስዔ ምላሽ የሚሰጥ ሰላማዊ መፍትሄ ካልተበጀ በስተቀር ሌላ አማራጭ መንገድ የለም፡፡ ግጭቶችንና ጦርነቶችን አንድ ወገን በኃይል አሸንፎ ወይም ተፋላሚውን አጥፍቶ በዘላቂ ሰላም ሊተካቸው አይችልም፡፡

አንድ ተፋላሚ ኃይል ሌላውን ተፋላሚውን በጦርነት ማጥፋት ቢችል እንኳ ሀሳቡንና ለጦርነቱ ምክንያት የሆነውን አስተሳሰብ ጨርሶ ማጥፋት አይችልም፡፡ ለማንኛውም ግጭት ምክንያት የሆነው ችግር ካልተፈታ በኃይል ዝም ለማለት የተገደደው ወገን በተለያየ መንገድ ግጭቱና ነውጡ እንዲቀጥል ያደርጋል፡፡ ሰላም በኃይል ሊመጣ እንደሚችል የሚሞግቱ ሀሳቦች ቢኖሩም የማንም ኃይል ዘላቂነት ስለማይኖረው ኃይል የዘላቂ ሰላም መንገድ አይሆንም፡፡ ሰላም ሊረጋገጥ የሚችለው በሰላማዊ መንገድ ብቻ ነው፡፡ ነውጥ ነውጥን፣ ጦርነት ጦርነትን ያስከትላል፡፡

### ተግባራት

- ዘላቂ ሰላም ዜጎች በሚገኙበት ሀገራዊ አውድ ውስጥ ከማንኛውም ዓይነት ሁከት ነጻ ከሚያደርጋቸው ማህረሰባዊ መዋቅር እንደሚመነጭ ተገንዘቡ፡፡
- ለሰላም መደፍረስ ዋናው ምክንያት የዜጎች የኑሮ ዋስትና፣ ፍትህና ክብር መነፈግ መሆኑን በመገንዘብ ለሰብዓዊ መብቶችና ፍትህ መከበር የሚበጅ አገልግሎት ስጡ፡፡
- ለሰላምና ደህንነት መጎልበት አስተዋጽኦ ማበርከት ለሚችሉ ተከታታይና ጥልቅ ትምህርታዊ ዘገባዎች ትኩረት ስጡ፡፡

---

[25] ሕዝቅያስ አሰፋ (2011)፤ የሰላምና እርቅ ትርጉምና መንገዶች፡ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እድገትና ከተፈጥሮ ጋር ባሉን ግንኙነቶች ላይ ያሏቸው አንድምታዎች፡፡ አዲስ አበባ፡፡

[26] Essia, Uwem (2020). Media for Peacebuilding Guidebook. Global Forum for the Defence of the Less Privileged: Cameroun

- ለሰላም መከበር የሚበጁ ባህላዊ እሴቶችን ሁሉም እንዲጋራ እድል የሚሰጡ የውይይቶች መድረኮችን አዘጋጁ፡፡
- ሰላምን የሚመለከቱ አካባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ እውቀቶች ማዳበርና መጋራት የሚያስችሉ ውይይቶችን አበረታቱ፡፡
- ሰላምን ከመስበክ ይልቅ ከማህበረሰባችሁ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር የሚጣጣሙ በእውቀትና መረጃ ላይ የተመሰረቱ ዘገባዎችን አቅርቡ፡፡
- በግጭት ወቅት ሁሉም ባለድርሻዎች ነውጠኛ ግጭቶች የሚያስከፍሉትን ሰብዓዊና ቁሳዊ ዋጋ ተገንዝበው ለሰላማዊ መፍትሄ ቁርጠኛ እንዲሆኑ ግፊት ሊያደርጉ የሚችሉ ዘገባዎችን ስሩ፡፡
- በግጭቶች ወቅት ሰላማዊ አማራጭ ፈታኝ ቢሆንም ወደ ዘላቂ ሰላም የሚወስድ ብቸኛ መንገድ መሆኑን ለሚያሳዩ ውይይቶች መድረክ አመቻቹ፡፡
- ለዘላቂ ሰላም ከሚሰሩ ተቋማትና ባለሙያዎች ጋር ተቀራርባችሁ ስሩ፡፡ የሰላም ተቋማት ድምጻቸውን እንዲያሰሙ እድል ስጡ፡፡
- መገናኛ ብዙሀን ስለ ሰላም መዘገብ ያለባቸው ጦርነት ሲቀሰቀስ ብቻ አለመሆኑን ተገንዝባችሁ በማንኛውም ጊዜ የሰላም ስጋት ሊሆኑ በሚችሉ አዝማሚያዎች ላይ ጥልቅ ዘገባዎች አቅርቡ፡፡

# የቃላትና ሀረጎች መፍቻ

## ሰላም

በግጭት ሙያዊ አዘጋገብ ውስጥ መሰረታዊ የሆነ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ጽንሰ ሀሳቡ በተለምዶ በነውጥና ጦርነት አለመኖር ብቻ የሚገለጽ አይደለም፡፡ ሰላም በማህበረሰብ ውስጥ እንደ ድህነት፣ የፍትህ እጦትና ተዋራጅነት ያሉ በማህበረሰብ መዋቅር ውስጥ ከተንሰራፉ የሁከት ሁኔታዎች ነጻ ከመሆን ጋር ይይዛል፡፡ የሚገኘውም የግጭቶች መንስዔዎችን በመፍታት ነው፡፡ ሰላም ከሰላማዊ መንገዶች ውጭ በነውጥ አማራጮች ሊገኝ አይችልም፡፡ ኃይል በመጠቀም ጥያቄዎች እንዳይነሱ ማፈን ቢቻልም ዘላቂ መፍትሄ ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ሰላም ሁሉን አካታች በሆነ ሰላማዊ መንገድ ብቻ ይረጋገጣል፡፡

## አካታችነት

አካታችነት ከግጭት ጽንሰሀሳብ ጋር ያለው ተዛምዶ ከሰላማዊ መፍትሄ ፍለጋ ጋር ይያያዛል፡፡ ግጭት የማህበረሰብ ልዩ ልዩ ክፍሎችን ስለሚመለከት የመፍትሄ ፍለጋ የተወሰነውን አካትቶ፣ ቀሪውን አግልሎ ሊሳካ አይችልም፡፡ የሚመለከታቸውን ሁሉ ማካተትን ይጠይቃል፡፡ የግጭት ሙያዊ አዘገጋብም በዘገባ ይዘቶች ውስጥ የሁሉንም ባለድርሻዎች ተወካዮች ድምጽ እንዲሰማ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## ዘገባ

ዘገባ ማለት ዜና፣ ዜና ትንታኔ፣ ሀተታ፣ ተራኪ ዘገባ፣ ርዕሰአንቀጽ፣ ሰናጅ ዘገባ (ዶክዩሜንታሪ)፣ ቀጥታ ቃለመጠይቅ፣ ትዕይንተ ውይይት (ቶክሾው)፣ የተደራስያን የቀጥታ የስልክ ወይይቶችና ሌሎችም መገናኛ ብዙሀን ይዘቶቻቸውን የሚያደራጁባቸውን የዝግጅት ዘውጎች ያጠቃልላል፡፡

## ድህረ-ግጭት

የ«ድህረ-ግጭት» ጽንሰ ሀሳብ ሁሉንም ሊያግባባ የሚችል አንድ ብያኔ ባይኖረውም፣ በሁከት፣ ነውጥና ጦርነት ውስጥ ያለፉ ማህበረሰቦች ግጭት ካስከተለባቸው ሰብዓዊ ቀውስ፣ ጥፋትና ውድመት ለማገገምና ለመረጋጋት፣ የመልሶ ማቋቋምና የመልሶ ግንባታ የሚያከናውኑበትን ጊዜ የሚገልጽ ትርጉም ይሰጠዋል፡፡ ይህም በማህበረሰቡ ውስጥ የግጭት ፍጻሜን ተከትሎ የሚመጣ ወስብስብ ሂደትንና የሚከናወኑ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ያካትተታል፡፡ ተቋማትን መልሶ ከማደራጀት፣ ከማዋቀርና ጥርጣሬን በማስወገድ መተማመንን፣ መግባባትንና ዘላቂ ሰላምን ከመገንባት ሂደት ጋር ይያያዛል፡፡

## ግጭት

በሰዎች የሀሳብና የፍላጎት ልዩነት ምክንያት የሚፈጠር የማይቀር ማህበራዊ ክስተት ነው፡፡ ሰዎች ግጭትን መቆጣጠርና መፍታት ይችላሉ፤ እንዳይኖር የማድረግ አቅም ግን የላቸውም፡፡ ክስተቱ ገሀድ መገለጫዎች ሳይኖሩት በማህበረሰብ ውስጥ ሊቆይ ይችላል፡፡ ሆኖም መፍትሄ ካልተበጀለት ወደ ሁከት፣ ነውጥና ጦርነት የማደግ እድሉ ሰፊ ነው፡፡ ግጭት በራሱ መጥፎም ጥሩም አይደለም፡፡ ሰዎች ለግጭት ምክንያት የሚሆኑ ችግሮችን መፍታት ከቻሉ ማህበረሰባቸውን የሚለውጥ መልካም አጋጣሚ ሊሆንላቸው ይችላል፡፡ ወደ ሁከትና ነውጥ ከተሸጋገረ ግን የጥፋትና የውድመት መጥፎ አጋጣሚ ይሆናል፡፡

## ግጭት ሙያዊ አዘጋገብ (የ)

የግጭት ሙያዊ አዘጋገብ ከመደበኛው የእለት ተእለት ዘገባ የበለጠ ሀላፊነትና ሙያዊ ክህሎት የሚጠይቅ አንድ የዘገባ ዘርፍ ነው፡፡ የበለጠ ክህሎትና ኃላፊነት የሚጠይቀው አለእውቀትና አለብቃት ከተያዘ በሰዎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችልና ግጭትን የማባባስ አሉታዊ ተጽእኖ ሊኖረው ስለሚችል ነው፡፡ ተግባሩ ማድረግ/አለማድረግን የመሰሉ ብዙ አሻሚ የስነምግባር መርሆዎች ያሉበት በመሆኑ የተለየ ዝግጅት ይፈልጋል፡፡ ስለ ግጭት ባህሪ በቂ መሰረታዊ ግንዛቤም ይሻል፡፡

# ማጣቀሻ ምንጮች


ሕዝቅያስ አሰፋ (2011)፤ የሰላምና እርቅ ትርጉምና መንገዶች፡ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እድገትና ከተፈጥሮ ጋር ባሉን ግንኙነቶች ላይ ያሏቸው አንድምታዎች፡፡ አዲስ አበባ፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፤ (2006)፤ ኣማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን/የተመድ የሴቶች ተቋም-ኢትዮጵያ (UNWomen) - ሥርዓተ-ጾታን ያገናዘበ የመገናኛ ብዙሀን አሰራር ሰነድ፡፡ (የህትመት ዓመትና ቦታያለተካተተበት)፡፡

ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፡፡ አዋጅ ቁጥር 1185/2012 ዓ.ም የጥላቻ ንግግርን እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ፡ ፡ ነጋሪት ጋዜጣ፤ ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር 26፤ መጋቢት 14 ቀን 2ሺ12 ዓ.ም፤ አዲስ አበባ፡፡

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት፡፡ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1265/2014፡፡ ነጋሪት ጋዜጣ ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፳ አዲስ አበባ ጥር 5 ቀን 2014 ዓ.ም፡፡

Adebo, Tarekegn & Tsadik, Hannah. Eds. (2016). Making peace in Ethiopia: Nine cases of traditional mechanisms for conflict resolutions. Addis Ababa: Life and Peace Institute, Peace and Development Centre.

ADONGO, Owade J., Ayodeji O. AWOBAMISEa† & Ogbonna CHIDIEBERE. "A peace journalism approach to understanding the role of the media in the land disputes in Kenya", in Journal of Social and Administrative Sciences. Vol. 5, Issue 2,

Berghof Foundation. (2017). National Dialogue Handbook: A Guide for Practitioners. Berlin: Berghof Foundation Operations GmbH

Bloh, Oscar. 2010. Strategic Communication for Peacebuilding a training guide How to use strategic communication on development objectives as a tool for peacebuilding. Search for Common Ground/Radio Peacebuilding Africa, New York.

Çiftcioğlu, Vasvi (2017). Peace Journalism: A Practical Handbook for Journalists in Cyprus. Naci Talat Vakfı and IKME: Nicosia.

Dubberley, Sam, Montaser Marai and Diana Larea – eds. (2017). Finding the truth amongst the fakes: Social newsgathering and news verification in the Arab World. Qatar: Al Jazeera Media Institute.

Essia, Uwem (2020). Media for Peacebuilding Guidebook. Global Forum for the Defence of the Less Privileged: Cameroun.

European Institute of Peace. Fake news misinformation and hate speech in Ethiopia: A vulnerability assessment. (12 April 2021).

Fischer, Dietrich. "Peace as a self-regulating process" in Webel, Charles and Johan Galtung(eds.). 2007. Handbook of Peace and Conflict Studies. Routledge: New York.

Huckerby, Martin. (2005). The Net for Journalists፡ A practical guide to the internet for journalists in developing countries. UNESCO: The Thomson Foundation.

Howard, Ross. (2008). Conflict Sensitive Journalism: A Handbook. (Special Edition Kenya). International Media Support.

Jenkins, Tony and Betty A. Reardon. "Gender and peace: Towards a gender-inclusive, holistic perspective" in Webel, Charles and Johan Galtung(eds.). 2007. Handbook of Peace and Conflict Studies. Routledge: New York.

Keen, Ellie; Georgesc, Mara; Gomes, Rui. (2014). A Manual for Combating Hate Speech Online Through Human Rights Education. Council of Europe. No Hate Speech Movement. Hungary.

Orgeret, Kristin Skare and William Tayeebwa (eds.) 2016. Journalism in conflict and post-conflict conditions: Worldwide perspectives. Nordicom: University of Gothenburg.

United Nations. 2019. United Nations Strategy and Plan of Action on Hate Speech. May 2019.

United Nations Development Program (n.d) Community Dialogue for Sustainable Peace: A Handbook for Generating Citizens' Engagement for Sustained Dialogue on Conflict Prevention, Social Cohesion and Integration. UNDP.

UNICEF. 2016. Peacebuilding, Education and Advocacy Programme in Ethiopia. UNICEF Evaluation Office: New York.

Webel, Charles & Johan Gultang, eds. (2007). Handbook of Peace and Conflict Studies. Routledge: London.

የኢትዮጵያ ብሮድካስተሮች ዘርፍ ማህበር
https://aebethiopia.com

የኢትዮጵያ አርታዕያን ማህበር
Email- editorsethiopia@gmail.com

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ምክርቤት
www.ethiopianmediacouncil.org

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሙያዎች ማህበር
Email - emmpaeth@gmail.com

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሙያ ሴቶች ማህበር
Email- emwa2014@yahoo.com

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን ባለሥልጣን
www.ema.gov.et/
Email- info@ema.gov.et

ዴስቲኒ ኢትዮጵያ
destinyethiopia.com

Design& Printed by : Eldel Printing 0960437353